# የጋብቻ ለውጥ መለማመጃ ሥርዓተ ክዋኔዎች በጃቢ ጠህናን ማኅበረሰብ
# Marriage Transformation Exercising Rituals in Jabi Tehinan District

**ስራዬ እንዳለው[1]፣ ዋልተንጉሥ መኮንን[2]፣ ደስታ አማረ[3]**
**Siraye Endalew, Waltenigus Mekonnen, and Desta Amare**

## አጠቃሎ

ጋብቻ በባሕርይው ሰዎች ጠበቅ ያለ ለውጥ የሚያካሂዱበት የሕይወት ዘመን የደረጃ ሽግግር ማድረጊያ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ፣ የተለያዩ ዓላማዎች ባሏቸውና ተከታታይ በሆኑ ሥርዓተ ክዋኔዎች ታጅቦ ይከበራል፡፡ ጋብቻ በጃቢ ጠህናን ወረዳ አሁንም ድረስ ከአስራ ስምንት ዓመት ዕድሜ የሚፈጸምባቸው ሁኔታዎች መኖራቸው ደግሞ ተጋቢዎች ላይ የሚደርሰውን ጫና ከባድና ውስብስብ ያደርገዋል፡፡ ሆኖም በወቅቱ በሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች አማካኝነት ሽግግሩን አካሂደው፣ ለውጡን ተቀብለው የማኅበረሰቡ አካል ሲሆኑ ይስተዋላል፡፡ ይህን ከጋብቻ በፊትና በኋላ ያለውን ተቃርኖ በማስማማትና ለውጡን በማላመድ የማኅበረሰቡ ህልውና ሚዛኑን ጠብቆ እንዲቀጥል ያስቻሉ ሥርዓተ ክዋኔዎችን የመረመረ ጥናት ባለመኖሩ ይህንን ጥናት ማካሄድ አስፈላጊ ሆኗል፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ በጋብቻ ወቅት የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ምን ምን እንደሆኑ መግለጽና ሚናቸው ምን እንደሚመስል ከጃቢ ጠህናን ወረዳ ማህበረሰብ ባህል፣ አኗኗር፣ ልማድና እምነት አንጻር ማሳየት ነው፡፡ በውስጡ ዋና ዋና የጋብቻ ሽግግር ሥርዓተ ክዋኔዎችን መግለጽ እና ለተጋቢዎች ለውጥም ሆነ ለማህበረሰቡ የሚያበረክቷቸውን ሚናዎች መተንተን የሚሉ ንዑሳን ዓላማዎችን ይዟል፡፡ ጥናቱ ዓይነታዊ ሲሆን መረጃዎች ከቀዳማይና ከካልአይ ምንጮች ተሰብስበዋል፡፡ ተሳትፏዊና ተሳትፏዊ ያልሆነ ምልከታ እንዲሁም ነጻ ቃለ መጠይቅ በመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀመ ሲሆን መረጃው የተግባራውያንን የንድፈ ሐሳብ ፈለግ በመደገፍ ተተንትኗል፡፡ የመረጃ ትንተናው ውጤት እንደሚያሳየው በጋብቻ ወቅት ከሰርግ ዋዜማ እስከ ጫጉላ ግላጭ ድረስ ምሪ የመፍታት፣ የወንድ ሙሽራን የመፈተን እና ቃል የማስገባት እንዲሁም የዙረሽ ግቢ ክዋኔዎች በሙሽሪት ወላጆች ቤት የሚፈጸሙ ሲሆን፤ ሙሽሮችን የተለየ ምግብ መመገብ፣ የጫጉላ ቤት ጨዋታ እና የጫጉላ ግላጭ ሥነ ሥርዓቶች ደግሞ በወንዱ ሙሽራ ወላጆች ቤት የሚቀጥሉ መሆናቸውን አመላክቷል፡፡ ሥርዓተ ክዋኔዎችም ጋብቻውን የማጀብ ወይም የማድመቅ፣ ሕክምና የመስጠት (የመፈወስ)፣ ባለጉዳይን ከሽግግሩ ጋር የማስማማት እና ለውጡን የማወጅ (ማረጋገጥ) ባጠቃላይ የጋብቻ ለውጡን የማለማመድ ሚናዎች እንዳሏቸው ጥናቱ አመላክቷል፡፡

**ቁልፍ ቃላት፡-** ጋብቻ፣ ለውጥ፣ ሥርዓተ ክዋኔ፣ የሰርግ ዘፈኖች፣ ጃቢ ጠህናን

---

[1] በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በፎክሎር ሦስተኛ ዲግሪ ተማሪ፣ በመዳ ወላቡ ዩኒቨርሲቲ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር መምህርት፣ Email: siraye3195@gmail.com

[2] በፎክሎር ፒ.ኤች.ዲ፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪ፡፡

[3] በፎክሎር ፒ.ኤች.ዲ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ባህሎች አካዳሚ ተመራማሪ፡፡

**Abstract**

Marriage is a phase of life in which humans go through drastic changes, and it is celebrated with a continuum of rituals with different objectives. The fact that marriage still takes place below the age of eighteen in the Jabi Tehinan district makes the pressure on married couples difficult and complicated. However, it can be seen that they have made the transition, accepted the transformation, and become a part of the society through the processes that take place at the time. It is necessary to conduct this research because there is no research that has examined the rituals that allowed the existence of the community to maintain its balance by harmonizing the contradiction between before and after marriage and adapting to the change. The main purpose of the study is to explain what the rituals that take place during marriage are and to show what their role is like in terms of the culture, lifestyle, customs, and beliefs of the Jabi Tehinan district community. It has the specific objectives of describing the major processes of marriage transition and analyzing the roles they contribute to the transition of couples and to society. The study is qualitative, and the data used primary and secondary sources. The research data were collected through participant and non-participant observation and open-ended interview methods. The research also used the functionalism theoretical framework to analyze data. The results of the data analysis show that during the marriage period, from the eve of the wedding to the wedding ceremony and honeymoon, the activities of untying the bridegroom, testing the bridegroom and making promises, and the circumambulation are performed at the bride's parents' house. He pointed out that feeding the brides a different meal, the wedding house game, and the ending honeymoon ceremony will continue at the home of the groom's parents. Rituals can accompany or highlight the marriage, provide treatment (heal), adapt the couple to the transition, and announce (validate) the transformation.

**Keywords:** Marriage, Transformation, Ritual, Jabi Tehinan District

## 1. መግቢያ

ጋብቻ በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ሰዎች ጠበቅ ያለ የሕይወት ደረጃ ሽግግርና ለውጥ የሚያካሂዱበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ፣ የተለያዩ ዓላማዎች ያሏቸውና በሂደት በሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ታጅቦ እንደየአካባቢውና እንደየባህሉ ይከበራል። በጃቢ ጠህናን ወረዳ ደግሞ አሁንም ድረስ ጋብቻ በልጅነት እድሜ የሚፈጸም መሆኑ ሽግግሩንና ተጋቢዎች ላይ የሚደርሰውን ጫና ከባድና ውስብስብ ያደርገዋል። ሆኖም ጋብቻው ሲፈጸም በሂደት በሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች አማካኝነት ተጋቢዎች ሽግግሩን አካሂደው እና ለውጡን ተቀብለው የማኅበረሰቡ አካል ይሆናሉ። የዚህ

ጥናት ትኩረትም በጋብቻ ወቅት የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ተጋቢዎች ለሚያካሂዱት ለውጥ ያላቸውን ሚና መመርመር ነው፡፡

በጋብቻ ወቅት የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ከጋብቻ በፊት የነበረን የተጋቢዎች ሁለንተናዊ ሁኔታ እና ከጋብቻ በኂላ የሚጠበቁባቸው ለውጦች አስማምተው፣ አስታርቀውና አላምደው የማኅበረሰቡ ህልውና ሚዛኑን ጠብቆ እንዲቀጥል ያላቸውን ሚና ለማሳየት ሲባል ጥናቱን ማካሄድ አስፈልጓል፡፡ የዚህ ጥናት ዋና አላማ የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔዎችን ሚና በጃቢ ጠህናን ወረዳ ማኅበረሰብ ባህልና እምነት ማሳያነት መግለጽ ሲሆን በጋብቻ ወቅት የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎችን መለየት እና ተጋቢዎች ለሚያካሂዱት ለውጥ ያላቸውን ሚና መተንተን የሚሉ ንዑሳን ዓላማዎች አሉት፡፡ ጥናቱ በጋብቻ ወቅት የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ምን ምን ናቸው? ለተጋቢዎች ለውጥም ሆነ ለማኅበረሰቡ የሚያበረክቷቸው ፋይዳዎችስ ምን ምን ናቸው? የሚሉ የምርምር ጥያቄዎችን መልሷል፡፡

ጥናቱ የተካሄደው በዐማራ ክልል፣ በምዕራብ ጎጃም ዞን ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል የጃቢ ጠህናን ወረዳ ማህበረሰብ ላይ ነው፡፡ ወረዳው ለጥናት የተመረጠበት ምክንያት ሰፊና በውስጡ ከሚገኙ አርባ አንድ ቀበሌዎች ውስጥ ሰላሳ ዘጠኝ ያህሉ የገጠር ቀበሌዎች በመሆናቸው የተለያየ የአየር ንብረትና መሰረተ ልማት ያላቸው ናቸው፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች በጋብቻ ወቅት የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎችን ቅርጽ፣ ዓላማና ይዘት የተለያየ እንዲሆን አድርገዋል፡፡ ለአብነት ያህል በቆላ እና በደጋ አካባቢዎች፣ መሰረተ ልማት (ትምህርት፣ ጤና፣ ትራንስፖርት…) በተዳረሰባቸውና ባልተዳረሰባቸው አካባቢዎች የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች የተለያዩ በመሆናቸው ሁሉንም ተደራሽ ለማድረግና ወካይ የሆነ መረጃ ለማግኘት ሲባል ነው፡፡

## 2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ጋብቻን ዋና ጉዳይ በማድረግ በተለያዩ የትምህርት መስኮች የተለያዩ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ የመጀመሪያው አንጻር ያለ ዕድሜ የሚፈጸምን ጋብቻ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊትና የልጆችን ሰብዓዊ መብት የሚጥስ ተግባር መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው (Guday, 2005)፡፡ እንዲሁም ያለ ዕድሜ ጋብቻ በተለይ በዐማራ ክልል ልዩ ልዩ ዞኖችና ወረዳዎች አሁንም ድረስ በስፋት የሚተገበር መሆኑን በመጠቆም በተጋቢዎች በተለይም ሴቷን ለልዩ ልዩ ግላዊ፣ ማኀበራዊና ስነ ልቡናዊ ጉዳቶች እንደሚዳርጉ ካሳዩ ጥናቶች መካከል (Zelalem, 2018)፣ Mikiyas(, Ansha and Others) እና (Vergroesen, 2017) ይጠቀሳሉ፡፡ ያለእድሜ ጋብቻ ከልጆች የትምህርት ሁኔታ፣ ጤና እና ሰብዓዊ መብት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር (Tilson & Larson, 2000)፣ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊት መሆኑን (Jensen & Thornton, 2003)፣ ሴት ልጆች ከጋብቻ በኂላ ለሚጠብቋቸው የሚስትነት፣ የእናትነትና ቤትን የማስተዳደር ኃላፊነቶች በአካል፣ በአእምሮና በስነ ልቡና ዝግጁና ብቁ ካመሆናቸው ጋር ተያይዞ ለብዙ ተጽዕኖዎች እንደሚዳረጉ (Otoo-Oyortey and Pobi, 2003)፣ (Ansell, 2005) እና (UNICEF, 2015) ገልጸዋል::

ያለ እድሜ ጋብቻ ያለእድሜ ለሚመጣ እርግዝና የሚዳርግ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለሕጻናትና ለእናቶች ሞት፣ ለድብርት እና ለኤች.አይ.ቪ.. ኤድስ እንደሚያጋልጥም (Molla, Berhane & Lindtjørn, 2008) እና (Raj, 2010) ጠቁመዋል፡፡ ጋብቻ በመፈጸማቸው ምክንያት ትምህርታቸውን በከፍተኛ ሁኔታ ለማቋረጥ መገደድ (Tilson & Larson, 2000)፣ ትምህርትን ካለመማር ጋር በተያያዘ የውሳኔ ሰጭነት ብቃት አለመኖር (Jensen & Thornton, 2003) እንደሁም ከጾታዊ ጉዳዮች ጋር ለተያያዙ የመብት ጥሰቶች ይጋለጣሉ (Otoo-Oyortey & Pobi, 2003)፡፡

ማኅበረሰቡ ያለእድሜ ጋብቻን ከሚፈጽምባቸው መሰረታዊ ምክንያቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ ማኅበረ-ባህላዊ እሴቶችን ለማስቀጠል፣ ሀብት ለማፍራት የልጆችን የወደፊት ህይወት ለማስተካከል፣ ተጨማሪ የእርሻ መሬት ለማግኘት፣ ዘርን ወይም ትውልድን ለማብዛት/ለማስቀጠል፣ በአንድ የሰርግ ድግስ ሌሎችን ታናናሾችንም በማጋባት ከሚወጣ ወጭ ለመቆጠብ፣ ሴት ልጆችን በድንግልና ጠብቆ ለባል ለማስረከብ፣ የስራ ድርሻቸውን ለማስተዋወቅ፣ ከሥርዓተ ጾታ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለማጠናከር ለማስጠበቅ፣ ከጋብቻ በፊት ከሚፈጸም የግብረ ስጋ ግንኙነትና እርግዝና ጭምር ለመጠበቅ፣ ዝምድና ለመመስረት፣ እውቀት ማነስ እና ድህነት ዋና ዋና ምክንያቶች መሆናቸውን አጥኝዎች (Guday, 2005; Zelalem, 2018) ጠቁመዋል፡፡ ያለ እድሜ ጋብቻ በሴቶች ጤና ላይ ከሚያሳድረው ተጽዕኖ ባሻገር በራስ መተማመን እንዳይኖራቸው፣ በኢኮኖሚ ከባላቸው እኩል ተጠቃሚ እንዳይሆኑ፣ ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡ፣ የውሳኔ ሰጭነት ሚና እንዳይኖራቸው፣ በጋብቻቸው እንዳይጸኑ፣ ያለእቅድ/አብዝተው እንዲወልዱ፣ ለኤች.አይ.ቪ. ኤድስ፣ ለፌስቱላ የአካል ጉዳት፣ በወሊድ ምክንያት ለሚያጋጥም ሞት ምክንያት መሆኑን ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን ገልጸዋል፡፡ በሴቶች ግላዊና ማኅበራዊ ሕይወታቸው ላይ ከሚያሳድረው ተጽዕኖ ባሻገር በአጠቃላይ በማህበረሰቡ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና አኗኗር ላይ ጫና አስከትሏል (Guday, 2005)፡፡

ያለ እድሜ ጋብቻ ከሴቶች ጤና እና ማኅበረ-ኢኮኖሚ ጋር ያለው መስተጋብር ምን እንደሚመስል ባሳዩበት ጥናት በምስራቅና በምዕራብ ጎጃም ዞኖች በሚገኙ ልዩ ልዩ ወረዳዎች ያለ እድሜ ጋብቻ በስፋት የሚፈጸም መሆኑን ገልጸው በሴቶች ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ስነ ልቡናዊና ተያያዥ የጤና ችግሮች ምክንያት የሆነባቸውን ተዛማጅ የሕይወት ቀውሶች መርምረዋል፡፡ የጥናቱ ግኝት ላይ እንደተገለጸው በጎዛምን ወረዳ ጋብቻ የሚፈጸመው ከአስር ዓመት እድሜ በታች ጀምሮ መሆኑን በመጥቀስ በልጅነት እድሜ ለሚከሰት እርግዝና ሴት ልጆች አካላዊ፣ አእምሯዊና ስነ ልቡናዊ ብስለትና ዝግጁነት ሳይኖራቸው አምጦ ለመውለድም ሆነ ልጆቻቸውን ለመንከባከብ ብቁ ባለመሆናቸው ምክንያት ጭምር ነው ይላሉ፡፡ በተጨማሪም ያለ እድሜ ጋብቻ በተጋቢዎች መካከል የዕድሜ ልዩነት እንዲኖር ምክንያት ነው (Zelalem, 2018;)፡፡ በተጨማሪም ያለ እድሜ ጋብቻ በልጅነት እድሜ እርግዝና ሊከሰት መቻሉ፣ ባል የሚፈልገውን ሁሉ ለማድረግ ሲል በሚስት ላይ አካላዊ ድብደባ እና ኃይል ሊጠቀም መቻሉ እንዲሁም በቤታቸው ውስጥ

ውይይትና ውሳኔ በሚፈልጉ ጉዳዮች ላይ እንደማይሳተፉም ጭምር ይገልጻሉ (Mikiyas, Ansha and Others, 2020)።

ሌላው ጋብቻ የተጠናበት ዕይታ በጋብቻ ማኅበረሰባዊ እሴቶች ላይ ትኩረት በማድረግ (Shambel, 2020) ጥናት ተጠቃሽ ሲሆን ጋብቻ በአርሲ ኦሮሞ ማኅበረሰብ ዘንድ ትልቅ እሴት መሆኑና ተጋቢዎችን ለዐዋቂነት (adult/elder) ደረጃ የሚያበቃቸው ሥርዓተ ክዋኔ መሆኑ ተጠቅሷል። በሌላ በኩል ሴት ልጆች፣ እናቶች፣ መምህራንና የሃይማኖት መሪዎች ያለ እድሜ በሚፈጸም ጋብቻ ዙሪያ ያላቸውን አመለካከት ላይ በተካሄደ ጥናት ላይ እንደተጠቀሰው አሉታዊ አመለካከት እንዳላቸው እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንደሚታገሉ፤ ሆኖም ማኅበር ወይም ዝክር በሚል የሽፋን ስም፣ የተጋቢዎችን እድሜ ጨምሮ በማስመዝገብና በሌሎች ዘዴዎች ጋብቻው አሁንም በስፋት እንደሚፈጸም፤ በዚህም ምክንያት የሚፈለገውን ያህል ለውጥ ማምጣት እንዳልተቻለ፣ አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት ግን ከራሱ ከማኅበረሰቡ ማኅበራዊ እውቀቶችና ብልሃቶች ዋጋ መስጠትና የመፍትሔ አካል ማድረግ እንደሚገባ ተጠቁሟል (Vergroesen, 2017)።

በልዩ ልዩ ሥርዓተ ክዋኔዎች ላይ ትኩረቱን በማድረጉ ከእኔ ጥናት ጋር የሚዛመደው ተጠቃሽ ጥናት በጉሙዝ ብሔረሰብ ልጃገረዶች ዘንድ የመጀመሪያ የወር አበባ መምጣትን ምክንያት በማድረግ የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ለማንነት ግንባታ፣ ለጋብቻ ሥነ-ልቦና እና ማኅበራዊ ደኅንነትና እድገት ያላቸውን አስተዋጽዖዎች የመረመረ ጥናት ይጠቀሳል። እነዚህም ለአካለ መጠን በደረሱ ሴቶችና በእናቶች ዘንድ ቅቡልነት ያሏቸው ሲሆኑ በአንጻሩ በታዳጊ ልጃገረዶች ዘንድ እንደ ጎጂ ልማዳዊ ተግባር ቢታዩም ሀገር በቀል ለሆኑ የእድገት (development) ንድፈ ሃሳቦች እድገትም አንድምታ እንዳሏቸው በጥናቱ ግኝት ተጠቁሟል (Wohabe, 2014)።

የእኔ ጥናት እላይ ከተቃኙት ጥናቶች ጋር የሚዛመደው ጋብቻ ላይ ትኩረቱን በማድረጉ ነው። እንዲሁም በጋብቻ ወቅት የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎችን ምንነትና ሚናቸውን ያሳየ፣ የቀደሙ ጥናቶች በስፋት የጠቆሟቸውን ከጋብቻ ጋር የተያያዙ አሉታዊ ጫናዎች በስርዓተ ክዋኔዎቻቸው አማካኝነት እንዴት አድርገው እንደሚቀንሱ/እንደሚጠብቁ ያመላከተ ነው። በአጠቃላይ ከጋብቻ ጋር ተያይዞ የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ለተጋቢዎችና ለማኅበረሰቡ ደኅንነት ያሏቸውን ሚና/ፋይዳ ከራሱ ከማኅበረሰቡ ባህላዊ፣ እምነታዊ፣ ቤተሰባዊ፣ አካባቢያዊ አንጻር የፈተሸ በመሆኑ ከቀደሙት የተለየ ያደርገዋል።

## 3. የጽንሰ ሐሳብና የንድፈ ሐሳብ መነሻ

### 3.1. የሥርዓተ ክዋኔ ምንነትና አስፈላጊነት

ሥርዓተ ክዋኔ (“ritual”) የሚለው ቃል “ritus” እና “ritualis” ከሚሉ ሁለት የላቲን ቃላት ጥምረት የመጣ ሲሆን ትርጉሙም የተለያዩ ቤተ እምነቶች ትዕዛዛት ሥነ ሥርዓታዊ ደንብ መሆኑና ጉዳዩ ራሱን ችሎ መጠናት የጀመረው በ19ኛው መቶ

ክፍለ ዘመን መጨረሻ የሃይማኖትን ምንጭ በመፈለግ ሂደት እንደሆነ ይገለጻል (Segal, 2006; 399)፡፡ ጥናቱ እንደተጀመረ ሃይማኖትን እና መስዋዕትን በመያያዝ ይጠና ነበር፡፡ መስዋዕት በሰውና በፈጣሪ መካከል ያለውን ግንኙነት ሰላማዊ ያደርገዋል ከሚል እሳቤ እንስሳትን በማረድ ለፈጣሪና በአውዱ ለተገኘው ሁሉ በማቅረብ ሥርዓቱን ይከውኑት እንደነበር ይገለጻል፡፡ ከዚያም በታሪክ፣ በስነ ሰብ፣ በሃይማኖታዊ ጥናቶች፣ በስነ ማኅበረሰብና በስነ ልቡና የምርምር መስኮች መጠናቱን ቀጥሏል (Mazama and Asante, 2009; 575-577)::

የሥርዓተ ክዋኔን ጥናት በማስተዋወቅ የመጀመሪያ እንደሆኑ የሚነገርላቸው Van Gennep (1909/1960) እንደገለጹት ሰዎች በሥርዓተ ክዋኔ የታጀበ የደረጃ ለውጥ ለማከናወን ባለ ሶስት እርከን መዋቅሮችን (መነጠል፣ ሽግግር እና ቅልቅል) ማለፍ አለባቸው ይላሉ፡፡ ቀጥሎ ወደ ጥናት መስኩ የተቀላቀሉት የስነ ሰብ ተመራማሪ Victor Turner ናቸው፡፡ Turner የGennepን ባለ ሦስት እርከን የመዋቅር ንድፈ ሀሳብ መሰረት በማድረግ ሥርዓተ ክዋኔ ድራማዊ መዋቅር ያለው የማኅበረሰብ ሂደት ነው ይላሉ፡፡ የሥርዓተ ክዋኔ ሂደት የማኅበረሰቡ መዋቅራዊ ክፍሎች ያሉት፣ የኃይል ሁኔታ እና እርስ በርስ ያላቸውን ዝምድና ያጠቃልላል፡፡ የሽግግር ጊዜውም ማህበራዊ ደንቦች የሚረጋገጡበት ወይም የሚለወጡበት ሊሆን ይችላል በማለት ያስረዳሉ (Turner, 1969; 95)፡፡ በተጨማሪም (Canda, 1988; 209) Gennep ጠቅሰው እንደጻፉት ሥርዓተ ክዋኔ የነበረን ሁኔታ የመለወጥ ሂደት ብቻ ሳይሆን ለውጥን የማረጋገጥና የመጠበቅ ሂደት ጭምር እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ለዚህም ዋነኛ ምሳሌዎች የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች (ወሊድ፣ ጋብቻና ሞት) ናቸው፡፡ ይህ ጥናትም የጋብቻ ሥርዓቶች ያላቸውን ሚና በጃቢ ጠህናን ማኅበረሰብ ማሳያነት መርምሯል፡፡

## 3.2. ሥርዓተ ክዋኔ እና ተግባራውያን

ሥርዓተ ክዋኔን ለማጥናት ከሚያስችሉ ንድፈ ሀሳቦች መካከል ቀዳሚው የተግባራዊያን እይታ ሲሆን በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ በአውሮፓውያንና በአሜሪካውያን የስነ ማኅበረሰብና የስነ ሰብ ተመራማሪዎች አማካኝነት እንደተጀመረ ይታወቃል (Bell, 1997፡ 23)፡፡ ትኩረቱም የሥርዓተ ክዋኔን የመከወን አላማና ለሚከውነው ማኅበረሰብ የሚኖረውን ጥቅም መግለጽ እንደነበር ያስረዳሉ፡፡ ሥርዓተ ክዋኔዎች ሲከወኑ መመልከትና ምን ማለት እንደሆኑ ራሳቸው ከዋኞችን በመጠየቅ እና መረጃ በመሰብሰብ ሲጠና ቆይቷል፡፡ በዚህም በክዋኔው የተሳተፉ ሰዎችን በመመልከትና ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃ ማግኘት ይችሉ ነበር፡፡ ተግባራዊያን አንድ ባህላዊ ክዋኔ ለማኅበረሰቡ ሥርዓት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ላይ ያተኩራሉ፡፡ ባህል ማኅበረሰቡ ቋሚና የተረጋጋ እንዲሆን እንደ አጥር ሆኖ ያገለግላል የሚል ሀሳብ አላቸው፡፡ በተጨማሪም ሥርዓተ ክዋኔ በአንድ ቡድን አባላት መካከል ያለውን ውስጣዊ ግንኙነት ያዳብራል፣ የማኅበረሰቡን ቡድናዊ እሴት ይጠብቃል፣ የአንድነት መንፈስን ያላብሳል ይላሉ፡፡

በአጠቃላይ ሕይወትን በተገቢውና በተረጋጋ መንገድ ለመምራት ይጠቅማል የሚል መሰረታዊ ሀሳብ አላቸው፡፡

የሥርዓተ ክዋኔን አጠናን ከተግባሩ ጋር አያይዘው ከሚገልጹት መካከል Emile Durkheim፣ Alferd Radcliffe-Brown እና Bronislaw Malinowski ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ባህል ለማህበረሰቡ የሚኖረውን ተግባር ሲገልጹ ማንኛውም ባህል የአንድ አካል አንድ የሰውነት ክፍል የሚጠቅመውን ያህል ለማኅበረሰቡ ይጠቅማል የሚል የጋራ የሆነ መሰረታዊ ሀሳብ አላቸው፡፡ ሆኖም ሦስቱም የየራሳቸው አቋም አላቸው፡፡ የ Bronislaw Malinowski የሀሳብ ፈለግ ባህላዊ ጉዳዩ ለሰው ልጅ የሚኖረው ስጋዊ፣ መንፈሳዊና ስነ ልቡናዊ ተግባር ላይ ያተኩራል፡፡ Radcliffe-Brown (1952; 10) ደግሞ ለቡድኑ ማኅበራዊ መዋቅር ለሚኖረው ሚና ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ Durkheim (1963; 386) ማኅበረሰቡ በሚጋራቸው አእምሯዊ መዋቅሮች ምክንያት ለሚኖረው ማኅበራዊ ትሥሥር ዋጋ ይሰጣል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ በየዘመኑ በተለያዩ ምሁራን የትኩረት አቅጣጫውን እየለየ የመጣ ቢሆንም ለእኔ ጥናት የ Bronislaw Malinowski እይታ የበለጠ ቅርበት አለው፡፡ Malinowski የ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተግባራዊ አተያይ አቀንቃኝ ሲሆኑ ሥርዓተ ክዋኔ የሰዎችን ድካም መቀነስ፣ ስሜትን መግለጥና የግለሰብንም ሆነ የማኅበረሰብን መሰረታዊ ፍላጎት ማርካት፣ ጭንቀትን፣ ፍርኃትን፣ ድብርትን፣ ጥርጣሬንና ሀዘንን የመቀነስ ሚና እንዳላቸው ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዱ ግለሰብ የሚያስፈልጉት ስነ ልቡናዊ ፍላጎቶች (ትውልድ/ዘር ቅጠላ፣ ምግብ፣ መጠለያ፣ ወዘተ.) የሚሟሉት በማኅበራዊ ተቋማት ነው የሚል እምነት አላቸው፡፡

እንደ Malinowski አስተሳሰብ አንድ ሰው ለመኖር ሊሟሉለት የሚገቡ አራት ነገሮች (መሰረታዊ ፍላጎቶች) ማለትም ምጣኔ ሀብት፣ ማኅበራዊ ደንብ፣ ትምህርት እና ፖለቲካዊ ተቋማት ሲሆኑ እነሱን ለማግኘት በባህሉ ውስጥ የሚተገበሩ ትዕምርታዊ ሥርዓቶች (እንደ ሃይማኖት፣ እምነትና እሴቶች) ሚናቸውን ይወጣሉ፡፡ እነዚህም የባህል ልዩ ልዩ ትዕምርቶች በሥርዓተ ክዋኔዎች አማካኝነት ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋሉ፡፡ ትዕምርቶች አንድን እውቀት ወይም ደንብ መግለጫ መሳሪያ ወይም የተግባቦት መንገድ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ፖለቲካዊ ትዕምርቶች የኃይልና የስልጣን መሳሪያዎች ናቸው (Malinowski in Firth 1973)፡፡

ይህንን ሀሳብ በመጋራት ትዕምርቶች ከማኅበረሰቡ ሂደት ጋር የተሳሰሩ በመሆናቸው፣ ከሚፈጸሙበት ጊዜ እና ከሁነቶች ቅደምተከተል አኳያ ለይቶ መተንተን አይቻልም (Turner, 1974፡ 20)፡፡ ከዚህ መሰረተ ሀሳብ በመነሳት በሥርዓተ ክዋኔ የሚገለጡ ትዕምርቶች በማኅበራዊ ድርጊቶች ላይ የራሳቸውን አሻራ ያሳርፋሉ፡፡ እንደ (Firth, 1971) ገለጻ ትዕምርቶች እምቅ አቅም ያላቸው የመረጃ አሐዶች ሲሆኑ ሥርዓተ ክዋኔን ከነ አውዱ ለመረዳት እንደሚያስችሉ የሚከተሉትን የትኩረት ነጥቦች አስቀምጠዋል፡፡ ከዋኞች ለክዋኔው የሚሰጡትን ፍች መግለጥ (an exegetical)፣ ከክዋኔው አውድ በመነሳት ትዕምርቶችን የማውጣት ጥበብ (an

operational) እና ነገሮችን በማወዳደርና በማነጻጸር የሚገኝ ፍች (the positîonal meaning) በሚሉ ሦስት የትንታኔ ደረጃዎች ከፋፍለው አሳይተዋል (Turner in Pentikainen, 1979፡ 159)፡፡

ትዕምርቶች በአንድ ቡድን አባላት መካከል ባለ ሁኔታዊ መስተጋብር ይገለጣሉ፡፡ በዚህ መሰረት ሀሳቦች ትዕምርታዊ ባሕርያት እና ፍች ወይም ትርጓሜ የሚኖራቸው በሂደት መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ በጊዜ ሂደትም ባህል ውስጥ ገብተው በሰው ሰውነት ላይ ስልጥነው ይታያሉ፡፡ ትዕምርቶች ልቅነትን ለመቆጣጠር፣ ለተጨማሪ መረጃ ምንጭነት ከመሆናቸውም ባሻገር ያላወቁትን ውስጣዊ ችሎታ እና ውጫዊ ማንነት የሚያገናኙ ድልድዮች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ሰብዕና የሚገነባው በባህል በተቃኘ ፍልስፍና አማካኝነት ነው፡፡ የፍች ሥርዓታቸው የተዋቀረውም ከሕይወት ልምድ በሚቀሰሙ ቅርጾች፣ ደንቦች፣ ጭብጦችና አቅጣጫዎች ነው (Pentikainen, 1979፡ 161)፡፡

## 3.3. የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔዎች ሚና

ጋብቻ አንድ ወንድና አንዲት ሴት በትዳር ባልና ሚስት ሆነው ለመኖር እንዲችሉ የሚፈጽሙት ሥነ ሥርዓት መሆኑን የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፣ 501) ያስረዳል፡፡ ይህንን ሀሳብ በማጠናከር ጋብቻ ወንድና ሴት ወደ አንድነት የሚመጡበት ሁነት ሲሆን ልጅ ሲወልዱ ደግሞ ሁለቱንም ቤተሰብ ወደ መመስረት የሚያውጅ የሚያደርግ መሆኑ በ (Royal Anthropological Institute, 1951, 110) ተገልጾ ይገኛል፡፡ ሁለቱም ሀሳቦች እንደሚያስረዱት ጋብቻ የተለያዩ ሰዎች ወደ አንድነትና አብሮነት የሚሸጋገሩበት ሁነት ነው፡፡ በጋብቻ የተለያየ ቤት ይኖሩ የነበሩ አንድ ቤት ወደ መኖር ይመጣሉ፡፡ ከፍ ሲልም በአስተሳሰብም ሆነ በዓላማ አንድ ወደመሆን ይሸጋገራሉ ይባላል፡፡

የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔዎች ዋና ተግባር አንድ ባለጉዳይ ከአንድ ማኅበራዊ ደረጃ ወደ ሌላ ሽግግር እንዲያደርግ ማድረግ እና አዲሱን ሚና ማለማመድ ነው፡፡ በኒዘርላንድ የሰርግ ሥነ ሥርዓቶች ላይ የተካሄደ ጥናት እንደሚያመለክተው የጋብቻ ሥርዓት ዋነኛ አላማ የሚና ሽግግር ማድረግ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡ በጥናቱ ላይ ሰዎች ከፍ ባለ ድግስ በታጀበ ጋብቻ፣ በቤተ ዕምነት የሚካሄድ ጋብቻ እና በጫጉላ ሽር ሽር አማካኝነት የእወቁልን ጋብቻን በመውሰድ ለምን በሥርዓተ ክዋኔታጅበው ጋብቻ እንደሚፈጽሙ አብራርተዋል፡፡ በሰርግ ሥነ ሥርዓት ወቅት ተጋቢዎች የደረጃ ለውጥ ዝግጅትና እርግጠኛ ያለመሆን ስሜትን (Status Preparation and Uncertainty) በአንድ ላይ ስለሚያስተናግዱ አንድም ለጋብቻው ያላቸውን ዝግጁነት ለማሳየት አንድም የሚሰማቸው ጥርጣሬ እንዲቀንስ ያግዛቸዋል፡፡ ጋብቻ በባህሪው በብዙ አጠራጣሪ ነገሮች የተሞላ ከመሆኑ ባሻገር ተጋቢዎች በጋብቻውና በትዳር አጋራቸው ዙሪያ፣ ከጋብቻ በኋላ የሚጠበቅባቸውን ሃላፊነት በመወጣትና ባለመወጣት ዙሪያ ጥርጣሬ ይሰማቸዋል፡፡ በተለይ በልጅነት እድሜ የሚፈጸም ጋብቻ በባሕርይው ለጭንቀትና ለግራ መጋባት የሚዳርግ ስለሆነ ሥርዓተ ክዋኔው እነዚህን ጥርጣሬዎችና ግራ መጋባቶች የመቀነስ ተግባር ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል

የሰርግ ሥነ ሥርዓት ሙሽሮች በትዳራቸው የሥነ ባሕርይ እርግጠኝነት (Behavioral Confirmation) እንዲኖራቸው ያግዛቸዋል፡፡ ከእነሱ በፊት የተጋቡ ጥንዶችን በማየት ጋብቻውን እንዲቀበሉት፣ እንዲያምኑበትና እንዲኖሩበት የማድረግ ኃይል አለው፡፡ ሙሽሮች በሥርዓተ ክዋኔው አማካኝነት የሚያደርጉት የሚና ሽግግር የማኅበረሰቡን ደንብ ከማረጋገጥም ባሻገር እውቅና ለሚሰጠው ማኅበረሰብም እንደ ማበረታቻ ነው፡፡ በተጨማሪም የሰርግ ሥነ ሥርዓት ሙሽሮች ለመጀመሪያ ጊዜ የግብረ ስጋ ግንኙነት የሚፈጽሙበት ጊዜ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ጥበቃ ለማድረግ በብዙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ይታጀባል (Salamone, 2004; 5)፡፡

## 4. የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት በዓይነቱ ዓይነታዊ ነው፡፡ ዓይነታዊ ጥናት በሰዎች አመለካከት፣ አስተሳሰብና ባሕርይ ላይ የሚያተኩር፣ በገለጻና በትንተና ላይ የተመሰረተ መሆኑን ምሁራን ይገልጻሉ (Dawson, 2007፡ 115)፡፡ በዓይነታዊ ጥናት የተመራማሪው ድርሻ የመረጃ ሰጭዎችን የህይወት ልምድ፣ አተያይ፣ አንጻርና ልምድ ማሰስና ማሳየት እንደሆነ ይገለጻል፡፡ ይህ ጥናትም ምድቡ ይህ ነው፡፡

### 4.1. የመረጃ ምንጮችና አሰባሰብ

የዚህ ጥናት መረጃዎች ከቀዳማይና ከካልአይ ምንጮች ተሰብስበዋል፡፡ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ወደሚጠናው ማኅበረሰብ በመሄድ፣ የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔዎች ሲፈጸሙ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በተተኳሪ የቡድን ውይይት አማካኝነት የተሰበሰቡበት ሲሆኑ፣ ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ደግሞ ልዩ ልዩ ቤተ- መጻህፍትን፣ ድረ-ገጾችን፣ መገናኛ ብዙኃንን፣ መጣጥፎችን በመጠቀም ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ እና ከጥናቱ አካባቢ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጽንሰ ሀሳቦችና ንድፈ ሀሳቦች የተገኙበት ነው፡፡

የዚህ ጥናት መረጃ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በተተኳሪ የቡድን ውይይት አማካኝነት ተሰብስቧል፡፡ ይህም በተለያየ ምክንያት በአንዱ ዘዴ መሰብሰብ ያልተቻሉ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ የመረጃውን ትክክለኛነት በማረጋገጥ፣ የመረጃ ሰጭዎችን ስሜት በመጠበቅ የተሻለ መረጃ እንዲገኝ አግዟል፡፡

ምልከታ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት ጥቅም ላይ ሲውል የጥናቱን ዓላማ ያገናዘበ መሆኑን፣ ተስማሚነቱንና ተገቢነቱን በመመዘን፣ ተጠኝው ማኅበረሰብ ጋር በመቆየት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ምርጫ ቦራቡር ቀበሌ የተከናወኑ ሁለት እና ዱምሪ ኪዳነ ምህረት ቀበሌ የተከናወነ አንድ በድምሩ ሦስት ባህላዊ ሰርጎች ላይ በመገኘት ተሳትፏዊና ተሳትፏዊ ያልሆነ ምልከታ በማድረግ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ የተደረገ ሲሆን ይህም በተጠኝው ማህበረሰብ ዘንድ እምነት እንዲኖረኝ፣ የተጋቢዎችን ትክክለኛ ስሜትና የማኅበረሰቡን መስተጋብር የተመለከቱ መረጃዎች እንዲገኙ አግዟል፡፡ እንዲሁም በቃላት የማይገለጹ የአካል እንቅስቃሴዎችን በማጤን እና ውስጣዊ ስሜቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን በተከሰቱባቸው ሁነቶች በቀጥታ

እንዲሰበሰቡ አግዟል፡፡ ተሳትፏዊ ያልሆነ ምልከታ ደግሞ በጋብቻ ሽግግር ወቅት የሙሽሮች አጠቃላይ ሁኔታ ለማጤን፤ ሥርዓተ ክዋኔዎችን በሙሉ ልብ ለመመልከት፣ ብዙ ሁኔታዎችን በአንድ ጊዜ ለመመልከት፣ ስለ ጉዳዩ ማስታዎሻ ለመያዝ፣ በክዋኔው ላይ ተፅዕኖ የሚፈጥሩ ነገሮችን ለመከታተልና ለመረዳት አስችሏል፡፡

በዚህ ጥናት የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ከምልከታ ቀጥሎ ቃለ መጠይቅ ወሳኙን ሚና ተጫውቷል፡፡ በመስክ ክንውን ወቅት በልጅነታቸው ጋብቻ በመፈጸማቸው ለተለያዩ ጫናዎች የተጋለጡ ወጣት ሴቶች እና እናቶች፣ ልጅ የዳሩ እናቶችና አባቶች፣ የጤና፣ የሴቶች፣ ህጻናት እና ወጣቶች ቢሮ ሰራተኞች፣ የትምህርት ቢሮ ባለሙያዎች የተውጣጡ ቁልፍ መረጃ ሰጭዎች ተሳትፈዋል፡፡

ለዚህ ጥናት ግብዓት የሆኑ ካልዓይ መረጃዎች ከተለያዩ ምንጮች ተሰብስበዋል፡፡ የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ የሚገልጹና የሚያብራሩ ጽንሰ ሀሳቦችና ንድፈ ሀሳቦች ከመጽሐፍት፣ ከመጣጥፎች፣ ለተለያየ ዓላማ እና ደረጃ ከተሰሩ ጥናታዊ ጽሑፎች፣ ጋዜጦች፣ ልዩ ልዩ ድረ ገጾች፣ የተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን ዜናዎች እና በማስረጃ የተደገፉ ዘገባዎች (Documentaries)፣ በምዕራብ ጎጃም ዞን እና በጃቢ ጠህናን ወረዳ ባህልና ቱሪዝም፣ ኮሚዩኒኬሽን፣ ግብርና ቢሮዎች አዘጋጅነት የታተሙ እና ያልታተሙ ጽሁፎችን በመጠቀም ነው፡፡ ከነዚህ ምንጮች የተሰበሰቡ መረጃዎች ጽንሰ ሃሳቦችን የመግለጽ፣ የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ ምንነት የማብራራት እና በቀደሙት እውቀቶች የመደገፍ ፋይዳ አበርክቷል፡፡

## 4.2. ጥናቱ የተካኼደባቸው ቀበሌዎች እና የመረጃ ሰጭዎች ናሙና አመራረጥ

ናሙና መምረጥ በዓይነታዊ ጥናት የተለመደ፣ ተመራማሪው መረጃ ሰጭዎችን በጥንቃቄ መርጦ የሚሰበስብበት ዘዴ መሆኑ ይገለጻል (Silverman, 2000፡ 7)፡፡ የጃቢ ጠህናንን ወረዳ ማህበረሰብ ወካይ የሆነ መረጃ ለማግኘት፣ ከአጠቃላይ አርባ አንድ ቀበሌዎች መካከል ስድስቱ የአየር ንብረትን፣ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥን እና የመሰረተ ልማትን ተደራሽነት መሰረት በማድረግ በአላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ስልት አማካኝነት ተመርጠዋል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በጋብቻ ወቅት የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች የተለያየ የአየር ንብረት፣ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ የመሰረተ ልማት ሁኔታ በተለያየ ሁኔታና ደረጃ ላይ የሚገኙ በመሆናቸው፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በጋብቻ ወቅት የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች የተለያዩ ናቸው፡፡

ከተጠኘው ማኅበረሰብ መካከል ሠላሳ አምስት መረጃ ሰጪዎች በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ የተመረጡበት ምክንያት ጉዳዩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸው ባለጉዳዮች፣ በተጋቢዎች ዙሪያ ያሉ ግለሰቦች ሆነው የዕድሜ፣ የትምህርት፣ የሙያ፣ የማኅበራዊ ደረጃ፣ የጾታ፣ የመኖሪያ ቀበሌ ልዩነትን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ከነዚህ መካከል የተሻለ የሃይማኖት፣ የባህል እና የታሪክ ዕውቀት ያላቸው እና ሐሳባቸውን እንደልብ የመግለጽ ችሎታ ያላቸው

አራት የሀገር ሽማግሌዎች፤ ከሰርግ ሽግግር ጋር የተያያዘ የሕይወት ተሞክሮ (ግለ ታሪክ) ያላቸው አምስት ሴቶች፣ በጠቅላላው ዘጠኝ ሰዎች በቁልፍ መረጃ ሰጪነት ተመርጠው መረጃ ሰጥተዋል፡፡

### 4.3. መረጃ አተናተን

በዓይነታዊ ጥናት አካሄድ የተሰበሰበውን መረጃ ከመተንተን በፊት ወደ ጽሑፍ መቀየር እንደሚገባ ይመከራል (Creswell, 2003፡ 20)፡፡ ቀጥሎም ከትንተናው የወጡ ዋና ዋና ጉዳዮች በመረጃ መደገፍና መዳበር ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህ ጥናትም የይዘት ትንተና ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በይዘት ትንተና በመጀመሪያ ወደ ጽሑፍ የተቀየረውን መረጃ በጥንቃቄ በማንበብ ለመረዳት ተሞክሯል፡፡ ቀጥሎ ከጭብጡና ከይዘቱ አኳያ ልየታ፣ ምደባ፣ ገለጻና ትንተና ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም በትንተናው ጎልተው የወጡ ጉዳዮችና ሀሳቦች ተጠቃለው ቀርበዋል፡፡

## 5. በጋብቻ ሽግግር ወቅት የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች

የጋብቻ ሽግግር በሰፊው ሲታይ ከዕጮኛነት ጊዜ ጀምሮ ሙሽሮች ተላምደው ጎጆ እስከሚወጡ ድረስ ያለውን ሂደት ያጠቃልላል፡፡ ሆኖም በዚህ ጥናት ሁሉንም ማካተት ቅርጹ የማይፈቅድ በመሆኑ፣ ዋናው ሽግግርና ለውጥ የሚካሄድበት ከሰርግ ዋዜማ ጀምሮ እስከ ጫጉላ ግላጭ[4] ድረስ ባለው ጊዜ የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ላይ ትኩረት ተደርጓል፡፡ በመጀመሪያ ሙሽሪት በወላጆቿ ቤት እያለች የጋብቻው ሥርዓተ ክዋኔ ክፍል የሆኑት ዳስ[5] የመስራት፣ የሙሽሪትን ምሬ[6] የመፍታት፣ ሙሽራውን የመፈተንና ቃል የማስገባት እንዲሁም የዙረሽ ግቢ ሥርዓቶች ይፈጸማሉ፡፡ ቀጥሎም ሙሽሪት ወደ ሙሽራው ቤተሰብ ከሄደች በኋላ በሚኖራት የጫጉላ ቤት ቆይታ ደግሞ ሙሽሮችን የተለየ ምግብ መመገብ፣ ጥበቃና እንክብካቤ ማድረግ፣ የጫጉላ ቤት ጨዋታ፣ ሙሽራ አጫዋች መመደብ፣ ሙሽራ ጠያቂ መላክና የጫጉላ ግላጭ ሥርዓቶች ይፈጸማሉ፡፡ በሙሽሪትም ሆነ በሙሽራው ቤት የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች በሴቷ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ እና የእሷን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል የሚከናወኑ ሲሆኑ እነሱም እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

### 5.1. በሰርግ ዋዜማ የሚከናወኑ ሥርዓተ ክዋኔዎች

በጃቢ ጠህናን ወረዳ ማኅበረሰብ በሰርግ ዋዜማ ከሚከናወኑ ሥርዓተ ክዋኔዎች መካከል ዳስ መስራት፣ ምሪ መፈታት፣ ዳውጃ መርገጥ፣ ሙሽራ መፈተንና ቃል ማስገባት እንዲሁም  ዙረሽ ግቢ በመባል የሚታወቁት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

---

[4] የሙሽሮች የጫጉላ ጊዜ የሚያበቃበት ሥነ ሥርዓት ነው፡፡
[5] ለእንግዶች ማረፊያ የሚሆን ጊዜያዊ አዳራሽ ሲሆን ሰርጉ እንደተጠናቀቀ ይፈርሳል፡፡
[6] ከከብት ቆዳ የተሰራ ልጃገረዶች በወገባቸው የሚታጠቁት መታጠቂያ ሲሆን ያንን የታጠቀች ሴት ልጅ ያላገባች መሆኗን ያመለክታል፡፡

### 5.1.1. ዳስ መሥራት

ዳስ መሥራት በወንዱም ሆነ በሴቷ ቤት የሚከናወን ሲሆን ቅዳሜና እሑድ ለሚከናወን ሰርግ ዓርብ ዕለት የሚዘጋጅ ለእንግዳ ማረፊያ የሚያገለግል ዳስ እና ለስጋ መቁረጫ የሚውል ሸንበቆ በአካባቢው አጠራር "ቃዣ" ተፈልጎ ይመጣል። በምልከታ[7] የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህ ጥናት መረጃዎች የተሰበሰቡባቸው የጋብቻ አውዶች የተከናወኑት ቅዳሜ እና እሁድ ስለነበር በሶስቱም ሰርጎች ላይ ቅዳሜ ጠዋት ሽማግሌዎች ተሰባስበው፣ የንስኃ አባት ጠርተው በሰርገኞች ቤት ፍሪዳው[8] ይጣላል። እዚያው ላይ ከትኩሱ ስጋ ሁሉም በተገኘበት በቅቤ ኩርፍ ጥሬ ስጋ እየዘለዘሉ እየጠበሱ ወይም ጥሬውን ይበላሉ። ለወጥ የሚሆንም ከላዩ ላይ ለሴቶች ይሰጧቸዋል። ምግቡ ተዘጋጅቶ በደረሰ ጊዜ ሁሉም ይበላል፤ ይጠጣል። በመጨረሻ ተመርቆ ሁሉም ወደ ቤት ገብቶ አታሞ/ከበሮ እየተመታ ይዘፈናል፣ ይጨፈራል። አቶ ለገሰ[9] እንዳሉት ይህም ክዋኔ የሰርጉ ስነ ሥርዓት በይፋ የተጀመረ መሆኑን የሚያበስር ነው ይላሉ። በመሆኑም በዚህ ጊዜ ሁሉም ካለበት እየመጣ ሰርጉን ይቀላቀላል፤ ሆኖም የመጣውም ያልመጣውም "መጥታችሁ ልጃችሁን መርቁ" እየተባለ አገርተኛው ሕዝብ በሙሉ ይጋበዛል ወይም ይጠራል።

### 5.1.2. ምሪ[10] የመፍታት ሥነ ሥርዓት

በሰርግ ዋዜማ ከሚከናወኑ ሥነ ሥርዓቶች መካከል ሁለተኛው ሙሽሪት የታጠቀችውን ምሪ የመፍታት ክዋኔ ነው። ወ/ሮ አስጨነቅ[11] እንደሚሉት ሙሽሪት የታጠቀችውን ምሪ የምትፈታላት ቀጣይ ልትዳር የምትችል ልጃገረድ ጓደኛዋ፣ ታናሽ እህቷ/ዘመዷ ልትሆን ትችላለች። ምሪውን በኃይል ከፈታችላት በኂላ በምትኩ መቀነት እንድትታጠቅ ይደረጋል ይላሉ። በተጨማሪም ምሪውን የፈታችላት ልጃገረድም ተረኛ መሆኗን ወዲያውኑ በወገቧ ታጥቃ ወይም በራሷ ላይ አስራ በአንገቷ ትዘፍናለች በማለት አስረድተዋል። በዚህ ጊዜም እንዲህ እየተባለ ለሙሽሪት ይዘፈናል።

ታጠቂው በቡጥጫ፣
አይገኝምና የእናት ዋንጫ።
ታጠቂው በጎመሮ፣
ከያዘ አይለቅም አባ ነብሮ።
ታጠቂው በገርንገደር፣
አይገኝምና ከአባት/ ከእናት ማደር።

[7] ምልከታው የተካሄደው በ23/06/2012 ዓ.ም፣ ምርጫ ቦራቡር ቀበሌ፣ 07/06/2012 ዓ.ም ዱምሪ ኪዳነ ምህረት እንዲሁም በዚሁ ቀን ምርጫ ቦራቡር ቀበሌ ላይ የተከናወኑ ሰርጎች ላይ ነው።

[8] የተቀለበ የእርድ ከብት ወይም ሰንጋ በሬ

[9] አቶ ለገሰ ምርጫ ቦራቡር ቀበሌ ነዋሪ ሲሆኑ ቃለ መጠይቁ የተካሄደው በ23/05/2012 ዓ.ም ነው።

[10] ምሪ ከከብት ቆዳ የሚሰራ ቀጭን ነገር ሲሆን ልጃገረዶች እስከሰርጋቸው ድረስ በወገባቸው የሚታጠቁት የልጅነት ምልክት ነው።

[11] ቃለ መጠይቅ፣ ወ/ሮ አስጨነቅ እንዳለው፣ ምርጫ ቦራቡር ቀበሌ ነዋሪ ሲሆኑ በልጅነት እድሜያቸው ጋብቻ ሲፈጽሙ የነበረውን አውድ የገለጹበት ነው። ቃለ መጠይቁ የተከናወነው በ23/08/2012 ዓ.ም ነው።

ታጠቂው በሣር ለምለም፣
አይገኝምና ወለም ዘለም፡፡[12]
ታጠቂው በጠቀርሻ፣
አይገኝምና የአባት ጉርሻ፡፡ እየተባለ ይዘፈናል (ወ/ሮ አስረሴ፣ 23/08/2013 ዓ.ም የተካሄደ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የምሪ መፍታት ሥነ ሥርዓቱም ሆነ በወቅቱ የሚከወኑ ቃል ግጥሞች የሚያሳዩት ሙሽሪት ምሪዋን ስትፈታ አብራ የምታጣቸው፣ በአንጻሩ ከሰርጉ በኋላ የሚጠብቋትና የምትጀምራቸው አዳዲስ ግላዊና ማኅበራዊ ሚናዎች መኖራቸውን ያሳያል፡፡ ይህንንም በቃል ግጥሙ ላይ በግልጽ እናገኘዋለን፡፡ ልጅነት እና ከልጅነት ጋር የተያያዙ ከእነሱ ጋር ማደር፣ በእጃቸው መጉረስ፣ በዋንጫቸው መጠጣት፣ ከእነሱ መዋል ማደር ወይም መኖርና የመሳሰሉ የለመደቻቸው የልጅነት ጊዜ የሕይወት ተሞክሮዎች ከፈታችው ምሪ ጋር ሳይመለሱ የሚቀሩ ናቸው፡፡ በምትኩ ከምትታጠቀው መቀነት ጋር የሚጀመሩ፣ ከማያውቁት ሰው ጋር መዋል ማደርና መኖር፣ ጾታዊ ግንኙነቶች፣ ራስን መቻል፣ ወዘተ. የመሳሰሉ ጉዳዮች እንደሚጠብቋት ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ ምሪ የመፍታት ሥነ ሥርዓት የሙሽሪት የልጅነት ጊዜ ማብቃቱን እና ለፍሬ የሚበቁበት ግንኙነት የሚጀመርበት መሆኑን የሚያውጅ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ከጋብቻ በፊት ታጥቃው የምትቆየው ምሪ የልጅነትና የድንግልና ምልክት መሆኑን በምትኩ በሰርጉ ዋዜማ የምትታጠቀው መቀነት ደግሞ ለአካለ መጠን መድረስን፣ ትልቅነትንና ሚስትነትን ተከትለው የሚመጡ ሚናዎች ማደሪያ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ሥርዓት ክዋኔ ሙሽሪት የሰርጉ ጊዜ መሆኑን ከማሳወቅ ጀምሮ ከሰርጉ በኋላ ስለሚጠበቁባት ግላዊና ማኅበራዊ ሚናዎች ፍንጭ የምታገኝበት በመሆኑ እና ለዚያም ዝግጅት የምታደርግበት በመሆኑ እንደ ለውጥ መለማመጃ ተወስዷል፡፡

### 5.1.3. ዳውጃ[13] የመርገጥ ሥነ ሥርዓት

ዳውጃ የመርገጥ ሥነ ሥርዓት በወንድም ሆነ በሴት ሙሽራ ቤት የሚከወን ነው፡፡ በሴት ሙሽራ ቤት በመገኘት በተከናወነ ምልከታ[14] ማረጋገጥ እንደተቻለው በሰርግ ዋዜማ ሙሽሪት በአዳዲስ አልባሳት እና ጌጣጌጦች አምራና ተውባ እኩለ ሌሊት ሲሆን ከተደበቀችበት ማጀት[15]፣ ተሸፋፍና እና ታዝላ፣ እልል እየተባለ፣ ጥላ

[12] ወለም ዘለም፡- በዚህ አውድ ልጆች ጠንከር ያለ ሥራ ሲሠሩ በብዛት ድካምና መዛል ስለሚታይባቸው ከሚሠሩት የማይሠሩት ይበዛል፡፡ ይህ በወላጆች ቤት ምንም ነውር የለውም፡፡ ነገር ግን በአማት ቤት ፈጽሞ የማይገባ ተግባር ነው፡፡

[13] ዳውጃ፡- ከቁጤማና ከቃጫ የሚሰራ የክብር መግለጫ ምንጣፍ ነው፡፡ አሁን አሁን ከስያሜው ባሻገር ትክክለኛ ስሪቱ ጠፍቷል፡፡ በምትኩ ሙሽሮች ከዘንባባ፣ ከከብት ቆዳ የተሰራ ማንኛውም ምንጣፍ ተነጥፎላቸው ሥርዓተ ክዋኔው ይካሄዳል፡፡

[14] ምልከታ፣ በቀን 07 እና 08/06/2012 ዓ.ም፣ ዱምሪ ኪዳነ ምህረት ቀበሌ፣ ቄስ ጸጋ የተባሉ አባወራ ልጆቻቸውን ሲድሩ በቤታቸው በመገኘት የተካሄደ ነው፡፡

[15] ማጀት የዋናው ቤት ክፍል ሲሆን የምግብ እህልና የቤት ውስጥ ቁሳቁስ የያዘ ነው፡፡ ማጀት የሴት/የሚስት ነው፡፡ የቤቱ አባወራ ሳይቀር ወደ ማጀት አይገባም፤ ነውር ነው፡፡ ሙሽሪት ከዚህ ክፍል የመውጣቷ ምክንያትም ከሴትነቷ ጋር የተያያዘ መሆኑን መረጃ ሰጭዎች ያስረዳሉ፡፡

ተዘርግቶላት ተሸፋፍና ወደ ሳሎን ወይም ወደ ዳስ እንድትመጣ እና እንድትታይ ይደረግና በተሰበሰበው ሰው መሃል በተነጠፈ ዳውጃ ላይ ያስቀምጧታል፡፡ በዚህ ጊዜ ሰርገኛ/ቤተ ዘመድ ሙሽሪትን ዙሪያዋን በመክበብ ይጨፍራል፡፡ ጭፈራው ተገስ ሲል ወላጆች፣ ታዳሚ ሽማግሌዎች፣ መነኩሴዎች ሙሽሮች ትዳራቸው እንዲቀና፣ ሀብታቸው እንዲባረክ ምርቃት ይቀርባል፡፡ ምርቃቱን የምትጀምረው ወላጅ እናት ስትሆን ቀጥሎ አባት ይመርቃል፡፡ ሽምግሌዎችና መነኩሴዎች ተራ በተራ ከመረቁ በኋላ በቄስ ጸሎት ሥርዓተ ክዋኔው ሲጠናቀቅ "ዳውጃ ረገጠች" ይባላል፤ ጋብቻውም እንደተፈጸመ ተቆጥሮ ሙሽሪት ለሙሽራው በክብር ትሰጠዋለች፡፡ በወቅቱ ከተከወኑ ምርቃቶች መካከል ቀጥሎ የቀረበውን እንደ ምሳሌ ማንሣት ይቻላል፡፡

> ጋብቻውን የእውነት ያርገው፣ ህጋቸውን ይባርክልን፣ ይልመዱ፣ ይክበዱ፣ ይውለዱ፣ ሀብታም ከብታም ያድርግልን፣ የተቀረጠላቸውን ሀብት ያቅናው፣ የአያታቸው የቅማታቸው ሀብት በእነሱ ላይ ይደር፣ ወልደው ከብደው እንዲኖሩ ያድርግልን፣ ከእናት አባታቸው ፈቃድ አያውጣቸው፣ ቤተ ክርስቲያን እሚሰሩ ሃይማታቸውን እሚጠብቁ ያድርጋቸው፣ ተምረው፣ አድገው፣ ቦታ እሚያስከብሩ፣ ዘመድ እሚጠቅሙ ያድርጋቸው፣ ደም መላሽ ያርጋችሁ፣ እንደ መንግስት መንግስት ያርጋችሁ፣ እንደ ካህን ካህን ያርጋችሁ (07/06/2012 ዓ.ም፣ ዱምሪ ኪዳነ ምሕረት የተካሄደ ምልከታ)፡፡

በዚህም ሙሽሮች ከጋብቻ በኋላ የሚጠብቋቸው፣ እንዲያከናውኗቸው የሚፈልጓቸው፣ እንዲሆኑ የሚመኙላቸው ተግባርና ምግባር በግልጽ ይታወቃል፡፡

## 5.1.4. ሙሽራ የመፈተንና ቃል የማስገባት ሥነ ሥርዓት

ሙሽራ መፈተንና ቃል እንዲገቡ ማድረግ በዋዜማው ሌሊት በሙሽሪት ወላጆች ቤት የሚፈጸም ነው፡፡ ከላይ በተገለጸው አውድ ላይ በተደረገ ምልከታ መሰረት ሙሽራው ከነሚዜዎቹ ከተጋበዘ በኋላ የሙሽራው ተወካይ የሆኑ የተመረጡ ሦስት ሚዜዎች በሽማግሌ እና በዘመድ አዝማድ ፊት ቀርበው ከሙሽራው ጋር ስላላቸው ዝምድና ይጠየቃሉ፡፡ ሙሽሪት በጫጉላ ቤት ስትቆይ ደኅንነቷ የተጠበቀ እንዲሆን ቃል ይገባሉ፡፡ በዚህ መሰረት ሚዜውም ለደኅንነቷ ቃል በመግባት የተረከባትን ሙሽራ ለሙሽራው እናት (ለአማቷ) ከልጃቸው እንደማይለዩላት ቃል አስገብቶ ያስረክባል፡፡

ይህ ሙሽራ የመፈተንና ቃል የማስገባት ሥነ ሥርዓት የሙሽሪት ቤተሰብና ዘመድ አዝማድ ፊት የሚከናወን በመሆኑ ሙሽሪት ደኅንነትና መረጋጋት እንዲሰማት ያደርጋል፡፡ ወላጆችም ሚዜዎች ለሙሽራው ያለውን የዝምድና ቅርበት ሲሰሙ፤ በጫጉላ ቤት ቆይታቸው ከአጠገባቸው እንደማይለዩ በንስኃ አባታቸው ሲገዘቱ ልጃቸው በሰላም እንደምትቆይ ዋስትና ይሆናቸዋል፤ እምነትም ይጥሉባቸዋል፡፡ በመሆኑም ሙሽሮች የጫጉላ ቤት ቆይታቸው በደህና እንደሚያልፍ እንዲያውም እንዲደሰቱና ጋብቻውን እንዲወዱት በማድረግ ለውጡንም የሚለማመዱበት ሥርዓተ ክዋኔ መሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም ሙሽራን መፈተንና ቃል ማስገባት ለሙሽሪት ደኅንነት እንደ ዋስትና የሚቆጠር በመሆኑ የሚጠብቋቸው ለውጦች ዝግጅት የሚያደርጉበት ተደርጎ ይታያል፡፡

### 5.1.5. የ"ዙረሽ ግቢ" ሥነ ሥርዓት

በሰርግ ዋዜማ ከሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች የመጨረሻው የዙረሽ ግቢ ሥነ ሥርዓት ነው፡፡ ከምልከታው መረዳት እንደተቻለው ዙረሽ ግቢ የሚከናወነው በሴት ሙሽራ ቤት ሆኖ የወንድ ሙሽራና ሚዜዎቹ ከገቡ በኋላ አብዛኛውን ሰዓት እየበሉ፣ እየጠጡና እየዘፈኑ አምሽተው በመጨረሻ ሙሽሪትን ተረክበው ወጥተው ከትንሽ ቆይታ በኋላ ተመልሰው ወደ ቤት የሚገቡበት ክዋኔ ነው፡፡ ሲገቡም ሙሽሮች (ባልና ሚስት) እጅ ለእጅ ተያይዘው በግ አርደው ተራምደውት ይገባሉ፡፡ በዚህ ወቅት ሚዜዎችም ሞቅ ያለ ዘፈን ዘፍነው በልዩ ሁኔታ የተዘጋጀላቸውን በቅቤ ኩርፍ እንጀራና የተመረጠ ወፍራም ጠላ እየተሻሙ በልተውና ጠጥተው ይወጣሉ፡፡ ከዚያም ሙሽሪትን ለቤተሰቦቿ አስረክበው ቀኑን ሙሉ ሲበሉ፣ ሲጠጡና ሲዘፍኑ ይውላሉ፡፡ በመጨረሻም በዋናው የሰርግ ዕለት ወደ እኩለ ሌሊት ገዳማ ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ሙሽራው ቤት ይዘዋት ይሄዳሉ፡፡ ሲሄዱም በተለያዩ ቡድኖች ሞቅ ያሉ የዘፈን ክዋኔዎችን ይከወናሉ፡፡ በሴቶች ቡድን ከሚከወኑ ቃል ግጥሞች መካከል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

> ሙሽራየ ሆይ፣
> እንዳንች አያምሩም ወይ፡፡
> ተውበሻል እቴ፣
> የብር መስታይቴ፡፡
> አጀባ ነው ሰውሽ፣
> በየት ልይሽ፡፡
> እንዳላይሽ፣
> ዳመናው ጣለ በላይሽ፡፡
> እንዳልነካሽ፣
> በወርቅ ሚዛን ተለካሽ፡፡ (ዱምሪ ኪዳነ ምሕረት ቀበሌ፣ 08/06/2012 ዓ.ም በተካሄደ ምልከታ የተገኘ መረጃ)፡፡

የዙረሽ ግቢ ሥነ ሥርዓት ሙሽሪት ከቤተሰብ መለየትን የምትለማመድበትና ጫናውንም መቋቋም እንድትችል ቅድመ ዝግጅት እንድታደርግ ያግዛታል፡፡

## 5.2. በጫጉላ ቤት የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች

በዚህ ክፍል ሙሽሪት ወደ ወንድ ሙሽራ ቤት ከሄደች በኋላ በጫጉላ ቤት የሚከናወኑ ሥርዓቶች ቀርበዋል፡፡ እነሱም ለሙሽሮች የተለየ ምግብ መመገብ፣ ሙሽራ አጫዋች መመደብ፣ የጫጉላ ቤት ጨዋታ፣ ሙሽራ ጠያቂ መላክና የጫጉላ ግላጭ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ በተናጠል ምን እንደሚመስሉ ከዚህ ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

### 5.2.1. ሙሽሮችን የተለየ ምግብ መመገብ

በጃቢ ጠህናን ማኅበረሰብ ዘንድ ሙሽሮች በጫጉላ ቤት ሲቆዩ የተለየና የተመረጠ ምግብ እንዲመገቡ ይደረጋል፡፡ እስከ ጫጉላ ግላጭ ድረስ እንደየሰው እና እንደየቤቱ

ሁኔታ ሙሽሮች ጭብጦ[16]፣ ዶሮ፣ ስጋ፣ ወተት፣ እንቁላል እየተመገቡ ይቆያሉ። በዚህ መንገድ ያለፉ ሴቶች በጫጉላ ቆይታቸው አንዳንዶች ጭብጦ ሌሎች ደግሞ ሙሉ ዶሮ እንዲሁም ስጋ፣ እንቁላልና ወተት እየተመገቡ እንደቆዩ አስረድተዋል። ይህም ጋብቻ ሙሽሪት ድንግልናዋን የምታጣበት አጋጣሚ በመሆኑ፣ በተፈጥሮ የነበረን ሙሉነት የሚያጎድል፣ አቅምን የሚያሳጣና ለሌላ ደረጃ የሚያደርስ በመሆኑ፣ ሰውነትን ለመጠገን፣ ድካምን ለመቀነስ፣ አቅምን ለማጎልበት ባጠቃላይ ያጣችውን ኃይል ለመተካት ሲባል እነዚህን ምግቦች መመገብ እንደሚገባት ይነገራል። ይህ በአማቷ ቤት የሚደረግላት እንክብካቤ በጋብቻው እንድትደሰትና ሁኔታውንም እንድትለምደው የሚያግዝ መሆኑ ይገለጻል።

### 5.2.2. ሙሽራ አጫዋች መመደብ

ሙሽራ አጫዋች በጫጉላ ቤት ቆይታ ሙሽሪትን የምትጠብቅ፣ በቅርብ የምትከታተል፣ የምታጊያጊጥ፣ የምትንከባከብ፣ ከሰውም ሆነ ከአካባቢው ጋር የምታላምድ የቅርብ ጓደኛ ናት። ሙሽራ አጫዋች ሙሽሪትን በጠዋት ወደ መጸዳጃ ቦታ ከመውሰድ ጀምሮ መሽቶ እስክትተኛ ድረስ አብራት ትሆናለች። ሙሽሪትን የምታጊያጊጣት፣ ምግብ የምታባላት፣ ስጦታ የምትቀበልላት፣ ምሥጢሯን የምታጋራት፣ የአዳር ገጠመኟን የምታወራት ጓደኛዋ ናት። የተመደበችው አጫዋች ያገባች ከሆነች በህይወት ልምድ የታገዘ ሙሽሪት ከባሏ ጋር ስለሚኖራት ግንኙነት፣ ስለ ጾታዊ ግንኙነቶች ጭምር ምክር ትሰጣታለች። የተለያዩ ሴቶች ያጋጠማቸውን ሁኔታ ባጋሩበት ተተኳሪ የቡድን ውይይት ላይ እንደገለጹት የአንዳንዶች አጫዋች ሁሉንም ነገር በድፍረት እንዲፈጽሙት የሚያበረታቱ ሲሆኑ የአንዳንዶች ደግሞ ማምለጥ የሚችሉባቸውን ብልሃቶች ልምዳቸውን አስደግፈው የሚጠቁሙ እንደነበሩ አስረድተዋል። ባጠቃላይ ሙሽራ አጫዋች ሙሽሪትን ከመንከባከብና ከማጊያጊያጥ ባሻገር በሕይወት ልምድ የዳበረ ምክር በመምከር ለሚመጠበቀው አዲስ የኑሮ ለውጥ የሚያዘጋጁ፣ የሚያበረታቱና ለውጡ ከደረሰ በኋላም የማጽናናት ተግባር ስላላቸው እንደ ጋብቻ ለውጥ ማለማመጃ ዘዴ ይወሰዳል።

### 5.2.3. የጫጉላ ቤት ጨዋታ "የደገም"

የደገም የተለመደ የጫጉላ ቤት ጨዋታ ሲሆን በጫጉላ ቤት የተገኙ ሰዎች ሁሉ የሚሳተፉበት፣ ሙሽሮችን እርስበርስ የሚያቀራርብና የሚያላምድ መሆኑ ይገለጻል። የአጨዋወት ሂደቱ ከሙሽሪት ጀምሮ ተራ በተራ አይናቸውን እየሸፈኑ ጭንቅላታቸውን በእጅ መምታትና የመታቸውን መለየት ነው፤ የመታውን እስከሚያውቅ ድረስ በተደጋጋሚ ይመታል (አቶ ዘለቀ፣ 23/05/2012 ዓ.ም የተካሄደ ቃለ መጠይቅ)። ይህ ጨዋታ ሁሉን አሳታፊ ስለሆነ ሙሽሪት በቀላሉ እንድትላመድና እንድትግባባ ይረዳታል። በሌላ በኩል ሙሽሪትን በእንግድነቷ ምክንያት በጣም እየመቱ እንዳያሳምሟትና እንዳያስከፏት ሙሽራው (ባል)

[16] ከአፍለኛ ጤፍ ዱቄት የተጋገረ ቂጣ በቅቤና በበርበሬ ታሽቶ የሚሰራ የምግብ አይነት ሲሆን በብዛት የአራስ ምግብ ነው። በምጥ የተጎዳን ወገብ ይጠግናል ተብሎ ይታሰባል።

በተቆርቋሪነት ስሜት ይጠብቃታል። ይህም ሙሽሪት ሙሽራውን እንድትቀርበው መንገድ ይከፍታል። የደገም የሙሽሮችን የጫጉላ ቤት ቆይታ አስደሳችና የማይረሳ ያደርገዋል ይላሉ። በተለይ የሙሽሪትን የእንግድነት ስሜት በመቀነስ በቶሎ እንድትላመድ የሚረዳ በመሆኑ የጋብቻ ለውጡን የመለማመጃ አንድ ብልሃት ይታያል።

### 5.2.4. ሙሽራ ጠያቂ መላክ

ሙሽሪት ካደገችበት ቤት ወጥታ፣ ከቤተሰቦቿ ተለይታ በአማቶቿ ቤት ስትቆይ የሚሰማትን የብቸኝነት ስሜት ለመቀነስና በቤተሰቦቿ ናፍቆት እንዳትጎዳ ለማድረግ በሄደች በሁለተኛው ወይም በሦስተኛው ቀን ታላቅ እህት/ አክስት/ ወንድም/ አጎት እንጀራና ጠላ፣ ዳቦ፣ ሎሚ፣ ሸንኮራ አገዳ በመያዝ ሄደው ልጃቸው በምን ሁኔታ ላይ እንዳለች የማየትና የመጠየቅ ልማድ ነው። ይህም ለሙሽሪት ደስታና መረጋጋት ከመስጠት ባሻገር ቤተሰብ እንዳላት እንድታስብና ተስፋ እንዳትናፍቅ ያስችላታል። በዚህ አጋጣሚ ቤተሰቦቿ የልጃቸውን መመቸት እና አለመመቸት ይረዳሉ። የሙሽሪትን ፊት አይተው እንዳልተመቻት ካሰቡ አንደኛ ሚዜውን ጠርተው “ልጃችን የከሳችው፣ የገረጣችው፣ የጠቆረችው ምን ሆና ነው? የሆነችው? በቤታችሁ ባገራችሁ እህል የለም?” በማለት ይጠይቃሉ። አያያዛቸውን እንዲያስተካክሉም ማስጠንቀቂያ የሚሰጡበት በመሆኑ ሙሽሪት ትረጋጋለች፤ ትደሰታለችም። ይህም ጋብቻው ከሚያስከትለው ለውጥ ጋር መጠነኛ ትውውቅ እያደረገች እንድትቆይ ይረዳል።

### 5.2.5. የጫጉላ ግላጭ

የጫጉላ ግላጭ የሰርጉ የመጨረሻው ሁነት ሲሆን ሙሽሮች ዋናውን የሙሽርነት ጊዜ ጨርሰው ወደ ማኅበረሰቡ የሚቀላቀሉበት ሥነ ሥርዓት ነው። በተለይ ሙሽሪት በጫጉላ ቤት ስትቆይ ከብዙ ነገሮች ተገድባ፣ ፊቷን በነጠላዋ ተሸፍና የምትቆይ በመሆኑ በዕለቱ ከነጠላዋ የምትገለጥበትና የጫጉላ ጊዜ አብቅቶ የምትወጣበት ሁነት በመሆኑ ሞቅ ደመቅ ባለ ሁኔታ ይከበራል። መረጃ ሰጭዎች እንደሚናገሩት ቀደም ባለው ጊዜ ሙሽሮች ጫጉላ ቤት የሚቆዩት ለአርባ ቀናት ያህል እንደነበረ እና አሁን አሁን እንደሁኔታው ለአስር እና ለአምስት ቀናት ይቆያሉ። በመሆኑም የሙሽሪት መልክና ቁመና የሚታው በዚሁ ዕለት ነው (አቶ ታምሩ ስንሻው፣ 25/05/2012 ዓ.ም በተካሄደ ቃለ መጠይቅ)። በዚህ ቆይታቸው ለአማቶቻቸው “ፍታይ” አልብሰው ለቤታቸው ስፌት አሚልተው ይገለጡ እንደነበር ይነገራል። በግላጭ ዕለት ሙሽሪት እንደተገለጠች የሰፋችው ስፌትና የፈተለችው ፈትል እየታየ ትመረቅና ትወደስ ነበር ይላሉ (አቶ ለገሰ፣ 23/05/2012 ዓ.ም በተካሄደ ቃለ መጠይቅ)። የግላጩ ሥነ ሥርዓት በወንድ ሙሽራ ቤተሰብ ዘንድ ከተከናወነ በኂላ በቀጥታ ወደ ሙሽሪት ቤተሰብ ሲደርሱ ዘመድ አዝማድ ተሰብስቦ እንዲህ በማለት እየዘፈኑ ይቀበሏቸዋል።

እንኳ መጣሽ እቴ፣
የብር መስታይቴ፡፡
እንኳ መጣህ አያ፣
ያ'ባይ ዳር ሱማያ፡፡

ከዚያም የወንድ ሙሽራ ሚዜዎች ያመጡትን የእጅ መንሻ በግ አርደው ወደ ውስጥ ይገባሉ፡፡ ለመስተንግዶ የተመረጡ ሚዜዎች የታረደውን በግ ሰርተው ለእንግዶች ያበላሉ፡፡

ግላጭ የጋብቻው ውጤት የሚታይበት በመሆኑ ሽግግሩ በሰላም ከተካሄደና የታሰበው ለውጥ ከተገኘ (የሙሽሪት ድንግልና ከተገኘ ማለት ነው፣ መልክ ከምግባር ያሟላች ከሆነች፣ ባለሙያ ከሆነች) እራሷ ሙሽሪትና ወላጆቿ የሚወደሱበትና የሚመሰገኑበት ነው፡፡ መረጃ ሰጭዎች እንዳስረዱት ምግብ ከተበላና ከተጠጣ በኋላ የሙሽሪት ወላጆች በዋናነት ሙሽሪት ከነ ክብሯ በመገኘቷ፣ ቆንጆ የወለዱና በጥሩ ምግባር ያሰደጉ በመሆናቸው፣ ባለሙያ ከሆነች እንዲህ እየተባሉ ይመሰገናሉ (አቶ ለገሰ እምሩ፣ 23/05/2012 ዓ.ም በተካሄደ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የሙሽሪት አባት ከላይ ይቀመጡ፣
የሙሽሪት እናት ከላይ ይቀመጡ፣
አሳድገዋታል እየቆነጠጡ፡፡
ሙሽሪት ለምዳለች፣
ከእናቷ ከአባቷ ባኋን ትወዳለች፡፡
ሙሽሪት ለምዳለች፣
እንዝርቴን ደጋኔን ላኩልኝ ብላለች፡፡

የጋብቻ ሽግግር አስገዳጅ ቢሆንም ለውጡ አዎንታዊ ትርጉም ስላለው ሙሽሮች በቶሎ እንዲቀበሉት ይፈለጋል፡፡ በተለይ ከጫጉላ ግላጭ በኋላ በሰርግ ዋዜማ እና ጫጉላ ቤት ይደረጉ የነበሩ እንክብካቤዎች ቀርተው ጫናው በተጋቢዎች ላይ ብቻ የሚቀጥል በመሆኑ ከባድ ይሆናል፡፡ ሆኖም ሙሽሮች ከትዳር አጋራቸው ጋር ተላምደው፣ ጎጆ ቀልሰው ወይም ቤት ሠርተው ከብደው ወልደው ራሳቸውን ችለው መኖር እስከሚጀምሩ ድረስ የወላጆቻቸው ክትትል አይለያቸውም፡፡ ለሙሽሮች የትዳርን፣ ራስ የመቻልን፣ የመላመድን፣ ቤት የመስራትን መልካምነት ከመምከር ባሻገር በተለያዩ መንገዶችም ድጋፋቸው አይለያቸውም፡፡

## 5.3. የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔዎች ሚና

በጃቢ ጠህናን ወረዳ ማኅበረሰብ ዘንድ በጋብቻ ሽግግር ወቅት የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ለሙሽሮችና ለቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ለአጠቃላይ ማኅበረሰቡ የሚያበረክቷቸው የተለያዩ አላማና ሚና እንዳላቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እነሱም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 5.3.1. የቅድመ ጋብቻ ዝግጅት የማድረግ ሚና

መረጃዎች እንደሚያሳዩት በጃቢ ጠህናን ወረዳ ማኅበረሰብ ዘንድ በጋብቻ ወቅት የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ተጋቢዎች ዝግጅት እንዲያደርጉ እንደሚያግዙ መረዳት ተችሏል፡፡ በተለይ ስለ ጋብቻውም ሆነ ስለሚያገቡት ሰው ምንም ዓይነት የቀደመ እውቅና ሳይኖራቸው የሚጋቡ ሙሽሮች ሥርዓተ ክዋኔዎች የሚያበረክቷቸው አስተዋጽዖዎች ቀላል አይደሉም፡፡ ወይዘሮ ድንቃየሁ እንዳሉት ከሆነ በተለይ ሴት ሙሽራ ታጭታ፣ ቀኑ ተቆርጦ ሁላ የጋብቻዋን ነገር አትሰማም፡፡ ልትዳር እንደሆነ የምትሰማው በድቁስ ሲቀመስ ወይም ዳስ ሲጣል ወይም ምሪ ስትፈታ ነው፡፡ ምክንያቱም ነውር ነው ልትዳር እንደሆነ ታወቀች ትጠፋብናለች ወይ አንድ ነገር ትሆንብናለች ተብሎ ስለሚሰጋ ሁሉም ነገር በሽሽግ/በድብቅ ነው ሚደረገው ይላሉ፡፡

አቶ ዘለቀ እንዳሉት ከሆነ ደግሞ ጋብቻ ከሙሽሮች እውቅና እና ፈቃድ ውጭ፣ በልጅነት እድሜ፣ ያለ ተጋቢዎች የቀደመ ትውውቅ የሚፈጸምባቸው ሁኔታዎች አሁንም ድረስ በመኖራቸው፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሁሉም ነገር የሚያልቀው በወላጆች ፍላጎት፣ ውሳኔና ስምምነት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ በተለይ ሴቶች ለበለጠ ጭንቀትና ግራ መጋባት ይዳረጋሉ፡፡ ሆኖም በጋብቻ ሽግግሩ ወቅት በሚፈጸሙ ክዋኔዎች፣ ቃል ግጥሞችና ምርቃቶች አማካኝነት ስለ ጋብቻው፣ ልጅነታቸው እንዳበቃ፣ ጾታዊ ጉዳዮችን ሊጀምሩ እንደሆነ፣ ልዩ ልዩ ግላዊና ማኅበራዊ ሚናዎች እንደሚጠብቋት ይነገራታል፡፡ በምሪ መፍታት ሥነ ሥርዓት ለሴቷ ስለ ጋብቻው ጥቁምታ ከመስጠት ባሻገር በስነ ልቡናም ያዘጋጃል፡፡ በምርቃት ሥነ ሥርዓት ደግሞ ጋብቻውን እንዲቀበሉ፣ እንዲለምዱ፣ እንዲከብዱ፣ እንዲወልዱ በግልጽ ስለሚነገራቸው ከጋብቻው በኋላ የሚጠብቋቸው ተግባራትና ለውጦች ዙሪያ መረጃ በመስጠት ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ የማድረግ ሚናቸውን ይወጣሉ፡፡

### 5.3.2. ሽግግሩን ማጀብ

የጋብቻ ሽግግር በልዩ ልዩ ሥርዓተ ክዋኔዎች ይታጀባል፡፡ ጋብቻ በባሕርይው ጠበቅ ያለ፣ ባለጉዳይን በኃይል አስገዳጅነት አፍርሶ እንደገና የሚሰራ፣ ወደቀጣዩ የሕይወት ሁነት የሚያሻግር፣ ሽግግሩ በሚገባ ካልታለፈ ለከፋ አደጋ የሚያጋልጥ ወሳኝ ሁነት በመሆኑ የሽግግር ወቅቱ አሳሳቢ መሆኑ በጽንሰ ሀሳብ ገለጻ ላይ ተጠቁሟል፡፡ የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔዎች ዋና ግብ ሙሽሮችን ወደ አንድነት ወይም አብሮነት ማሸጋገር፣ የተጋቢዎችን የመጀመሪያ የግብረ ስጋ ግንኙነት ማክበር፣ ከጾታዊ ባሕርያትና ደንቦች ጋር የተያያዙ የአመለካከት ለውጦችን ማምጣትና ግለሰቡን በጾታዊ ባሕርይው ላይ ለውጥ እንዲያካሂድ መርዳት ነው፡፡ የጃቢ ጠህናን ሰርግ ወቅት በዋናነት ከዋዜማ ጀምሮ እስከ ጫጉላ ግላጭ ድረስ የሚከናወኑ ምሪ መፍታት፣ ዳውጃ መርገጥ፣ ዙረሽ ግቢ፣ ወዘተ. የመከናወናቸው ዋና ዓላማ ሙሽሮች ህጻናት ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ የጋብቻ ሽግግሩ የሚያስከትላቸውን አዳዲስ ለውጦች የማስተናገድ አቅማቸው አስጊ በመሆኑ ይህንን ስጋት ለመቀነስና መልካም ውጤት እንዲገኝ ሲባል ነው፡፡

የጋብቻ ሥርዓት ክዋኔዎች በሽግግር ወቅቱ የሚፈጠሩ ጥርጣሬዎችና ግራ መጋባቶች እንዲቀንሱና ሙሽሮች በትዳራቸው እርግጠኛ እንዲሆኑ፣ ጋብቻውን እንዲቀበሉት፣ እንዲያምኑበትና እንዲኖሩበት ያግዛሉ፡፡ ሙሽሮች በሥርዓት ክዋኔው አማካኝነት የሚያደርጉት የሚና ሽግግር የማኅበረሰቡን ደንብ ከማረጋገጥም ባሻገር እውቅና ለሚሰጠው ማኅበረሰብም እንደ ማበረታቻ ነው፡፡

### 5.3.3. ጥበቃ ማድረግ

ከሰርግ ዋዜማ ጀምሮ የሚከናወኑ ሥርዓተ ክዋኔዎች ዋና ሚና ሙሽሮችን ከተለያዩ እክሎች ለመጠበቅ ነው፡፡ አቶ ለገሰ እንዳስረዱት ከሆነ የሙሽራውን ሚዜዎች ጥያቄ በመጠየቅ አስተዋይነታቸውን መመዘን እና በሽማግሌ ፊት ቃል ማስገባት ዋና አላማ እንዲሁ ሰርጉን ለማድመቅ ሳይሆን ሙሽሪት በአማቶቿ ቤት በደኅና እንድትቆይ ለማድረግ ነው፡፡ ቀጥሎም  በጫጉላ ቤት ሲቆዩ የሚደረጉላቸው እንክብካቤዎች ዋና አላማ ሙሽሮች "የመጀመሪያ" ተብሎ የሚታመነው የግብረ ስጋ ግንኙነት የሚፈጸምበት በመሆኑ ሙሽሮችን ለማዘጋጀት ቀጥሎም ጉልበት ለመተካት ሲባል መሆኑን መረጃ ሰጭዎች ያስረዳሉ፡፡ ስለዚህ በጋብቻ ወቅት የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ዋና ዓላማ የሽግግር ወቅቱ በሰላም እንዲጠናቀቅና የሚጠበቀው ወይም የሚፈለገው አዎንታዊ ለውጥ እንዲገኝ በአጠቃላይ የጋብቻ ሽግግሩ ግቡን እንዲመታ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑ ተደጋግሞ ይገለጻል፡፡

### 5.3.4. ሕክምና መስጠት (መፈወስ)

የጋብቻ ሽግግር ወቅት ባለጉዳይን ከነበረውም ሆነ ወደፊት ከሚሆነው ማንነት ውጭ ስለሚያደርግ ወቅቱ ጭንቀትና ግራ መጋባት የሞላበት ነው፡፡ በመሆኑም በወቅቱ የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ይታከማሉ፡፡ ጭንቀትን በመቀነስ፣ ሽግግሩ የግድ እንደሆነ እና እምነት እንዲያድርባቸው፣ ጤናማ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ጉልህ ሚና ይጫወታሉ፡፡

በጋብቻ ሽግግር ወቅት የሚፈጸሙ ክዋኔዎች የማከምና የመፈወስ ሚና እንዳላቸው ይነገራል፡፡ አስጊ እና አሳሳቢ የሆነው የሙሽርነት ጊዜ በሰላም አልፎ የታሰበው ውጤት መጥቶ ስነ ልቡናዊ እረፍት እንዲገኝ ከላይ የቀረቡት ክዋኔዎች ይፈጸማሉ፡፡ በዋናነት በሾተላይ ምክንያት በልጅ ሞት የተፈተኑ ወላጆች ልጃቸውን በመዳር ጭንቀታቸውን ይቀንሳሉ፡፡ መረጃ ሰጭዎች እንደተናገሩት ልጆች በሰርጋቸው ወቅት ዳውጃ ሲረግጡ፣ ምሪ ሲፈቱ፣ በቤቱ ሲዘፈን ደስታ ሲሆን ባካባቢውም ያለ ርኩስ መንፈስ ይወገዳል (ቄስ ጸጋ፣ 09/06/2012 ዓ.ም የተካሄደ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ይህም አስተሳሰብ ሰዎች ሥርዓተ ክዋኔዎችን ካልፈጸሙ ጥሩ ያልሆነ ወይም ጎጅ ነገር እንደሚደርስባቸው ስለሚያስቡ ይህንን የፍርሃትና የጭንቀት ስሜት አስወግደው መረጋጋት እንዲሰፍን የተለመዱ ክዋኔዎችን የሚከውኑ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሀሳብ ነው፡፡ እኒሁ መረጃ ሰጭ ልጆቻቸውን ሲድሩ በመገኘት በተካሄደ ምልከታ እድሜያቸው የመጀመሪያዋ ስምንት፣ ሁለተኛው ስድስት እና ሶስተኛዋ

አራት ዓመት መሆናቸውን ማየት ተችሏል፡፡ በዚህ እድሜያቸው የመዳራቸውን ዋነኛ ምክንያት ሲገልጹ "በየጊዜው ባለቤቴንም ሆነ እኔን ሲያስደነግጠን የኖረ አጋንንት እንዲርቀን ብለን ነው" ይላሉ፡፡ ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው በወቅቱ የሚከወኑ ሥርዓተ ክዋኔዎች ይህን ውስብስብነትና ጭንቀት የመቀነስ ሚና ያበረክታሉ፡፡ ከሙሽሮች የሚጠበቁ ኃላፊነቶችንና ሚናዎችን በማስተዋወቅና በማላመድ በአጭር ጊዜ ጋብቻውን እንዲቀበሉ ያግዛሉ፤ የደኅንነት ማስጠንቀቂያ ይሰጣሉ፡፡

### 5.3.5. ተጋቢዎችን ከሽግግሩ ጋር ማለማመድና ማስማማት

የጋብቻ ሽግግር ግላዊ ደረጃ እና ሚና ከመለወጥ ባሻገር ከአዳዲስ ሁኔታዎች ጋር መገናኘትና መላመድ አልፎም አብሮ መኖር የሚጀመርበት በመሆኑ ውስብስብነቱ ከፍ ይላል፡፡ ሆኖም በወቅቱ የሚከወኑ ሥርዓተ ክዋኔዎች ይህን ውስብስብነት በመጠኑም ቢሆን ቀለል የማድረግ ሚና ይኖራቸዋል፡፡ ሥርዓተ ክዋኔዎች ለባለጉዳዮች ሃላፊነትን በማስተዋወቅ በአጭር ጊዜ ጋብቻውን መቀበል እንዲችሉ ያግዛሉ፤ በዚህም የደኅንነት ማስጠንቀቂያ ይሰጣሉ፡፡ በምልከታ[17] ማየት እንደተቻለው ሙሽሮች በተገዙላቸው አልባሳት እና ጌጣጌጦች አምረው፣ ተውበውና ደምቀው ዳስ ውስጥ በተሰበሰበው ሰው መሃል በተነጠፈ ዳውጃ ላይ ተቀምጠው ይመረቃሉ፡፡ ምርቃቱም የተለያየ ይዘት ያለው ሲሆን በዋናነት ትዳራቸው እንዲቀና፣ ሀብታቸው እንዲባረክ፣ ከመመኘት ባሻገር የሚጠብቃቸውን ግላዊ እና ማኅበራዊ ሃላፊነትም የሚጠቁም ነው፡፡ ምርቃቱን የምትጀምረው የሙሽራ ወላጅ እናት ስትሆን አባት ይቀጥልና ሽምግሌዎች ከዚያም መነኩሴ መርቆ በቄስ ጸሎት ይቋጫል፡፡ ከዚያም ሙሽሮች ሲወጡ ሴቶችና ወንዶች በተለያየ ቡድን ሞቅ ያለ ዘፈንና ጭፈራ ይከወናል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ በሴቶች ቡድን የተከወነ ክዋኔ ለማሳያነት ቀርቧል፡፡

ሙሽራየ ሆይ፣
እንዳንች አያምሩም ወይ፡፡
ተውበሻል እቴ፣
የብር መስታይቴ፡፡
አጀባ ነው ሰውሽ፣
በየት ልይሽ፡፡
እንዳላይሽ፣
ዳመናው ጣለ በላይሽ፡፡
እንዳልነካሽ፣
በወርቅ ሚዛን ተለካሽ፡፡

እነዚህ ክዋኔዎች ሙሽሮችን ማዕከል ያደረጉ በመሆናቸው በሽግግር ወቅቱ ከሚሰማቸው ጭንቀት እረፍት ያገኛሉ፡፡ ነገር ግን እንክብካቤው ከቤቷ እስከምትወጣ እና በአማቷ ቤትም እስከ ግላጭ ድረስ ብቻ የሚቆይ ነው፡፡ ከዚያም ሰርጉ

[17] ዱምሪ ኪዳነ ምህረት፣ 07/06/ 2012 ዓ.ም በተከናወነ ሰርግ ላይ የተካሄደ ምልከታ

ያስከተለውን ጫና ተቋቁማ እንድትቀጥል ይፈረድባታል፡፡ ታዳጊ ሰብለ[18] በሰርጓ ወቅት የተሰማትን የተደበላለቀ ስሜት እንዲህ በማለት ታስታውሳለች፡፡

> የኔ ሰርግ መሆኑን ስሰማ ደስ አለኝ፡፡ ምክንያቱም ብዙ ነገር ተገዝቶልኝ ነበር፡፡ ልብስ፣ ጫማ፣ ነጠላ፣ ሻሽ፣ ቅባት፣ ማበጠሪያ፣ ኩል፣ ሽቶ ሳሙና ሳይቀር ሲገዛልኝ ደስ ብሎኝ ነበር፡፡ በዚያ ላይ እኔ ስራ አልሰራም፣ ጓደኞቼ ያጫውቱኛል፣ ይንከባከቡኛል፡፡ እስከምለያቸው ድረስ ስስቅ ስጫወት ነበር፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ መዳሬን የጠላሁት ለጥሎሽ የመጣውን ቦላሌ[19]፣ ባርኔጣ፣ ካፖርት ስለባብስ ነው፡፡

የጃቢ ጠህናን ባህላዊ ሰርግ ዙረሽ ግቢ በተባለ ክዋኔ ሴቷ ለመጀመሪያ ጊዜ ከቤተሰቦቿ ትነጠላለች፡፡ ከአዳዲስ ሰዎች ጋር መቆየትም ትጀምራለች፡፡ ይህ ጊዜና ሁኔታ ሙሽሪትንና ሙሽራውን፣ እንዲሁም ሙሽሪትንና ሚዜዎቹን የማስተዋወቅ እድል ይፈጥራል፡፡ በምልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ዙረሽ ግቢ የሰርጉ ክዋኔ አካል ሲሆን ወንድ ሙሽራ በመጀመሪያው ቀን ሌሊት መጥቶ ሲበላ፣ ሲጠጣ፣ ሲዘፍን አድሮ ወደንጋት ወይም አስራ አንድ ሰዓት አካባቢ ሙሽሪትን ይዘው ይወጣሉ፡፡ ከዚያም ብዙ ሳይርቁ አንድ ዛፍ ስር ይቆዩና ተመልሰው መጥተው በግ አርደው፣ በድምቀት ዘፍነው፣ የቀረበላቸውን ቅቤ ኩርፍ ተሻምተው በልተው ወደተዘጋጀላቸው ጫጉላ የሚገቡበት ክዋኔ ነው፡፡ ከዚያም ሙሽሪትን ጓደኞቿ ወደቤተሰቦቿ ከጫጉላ ቤት ያመጧትና ቆይታዋ እንዴት እንደነበር ይጠይቋታል፡፡ በቆይታዋ የገጠማት ችግር ካለም ለቤተሰቦቿ ስለምትናገር በመጨረሻው ስንብት ያስጠነቅቁላታል፡፡ ዙረሽ ግቢ ሙሽራዋ በትንሹም ቢሆን መለየትን እንድትላመድ እና ከአዳዲስ ሰዎች ጋር እንድትተዋወቅ ይረዳታል፡፡ ይህም በአንድ ጊዜ ወደማታውቃቸው ሰዎች በመሄዷ የሚደርስባትን ጭንቀት በመጠኑም ቢሆን ይቀንስላታል፡፡

ከላይ ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ሽግግር ሁለት ተከታታይ የሆኑ የማይተዋወቁ ሁኔታዎችንና ማንነቶችን ለማገናኘት፣ አሮጌውን ትቶ፣ አዲሱን ይዞ ለመቀጠል የሚያስችል ሂደት በመሆኑ በወቅቱ የሚፈጸሙ ክዋኔዎች ተጋቢዎችን ለለውጥ የማዘጋጀት፣ ከአዲሱ ደረጃ ጋር የማገናኘት፣ የማይተዋወቁ ሰዎችን፣ ማንነቶችንና አካሎችን በማለስለስና በማስማማት የሚፈለገው ለውጥ እንዲካሄድ ትልቁን ድርሻ ይወጣሉ፡፡ ተጋቢዎች ለሽግግሩ ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ፣ ሽግግሩን በድፍረት እንዲያካሂዱና የተገኘውን ለውጥ መቀበል እንዲችሉ ባጠቃላይ ለውጡን ተላምደው እንዲቀጥሉ ይረዷቸዋል፡፡

የጋብቻ ሽግግር የተጋቢዎችን ግላዊና ማህበራዊ ደረጃ ከመለወጥ ባሻገር ጾታዊ ግንኙነቶች የሚጀመሩበት በመሆኑ ውስብስብነቱ ከፍ ይላል፡፡ ሆኖም ሥርዓተ ክዋኔዎች ከሙሽሮች የሚጠበቁ ሃላፊነቶችንና ሚናዎችን በማስተዋወቅና በማላመድ

---

[18] ሰብለ የሚለው ስም በአጥኚዋ የወጣ ሲሆን መረጃውን በሰጠችበት ጊዜ የ15 ዓመት ታዳጊ ነበረች፡፡ በ8 ዓመት እድሜዋ ያገባች፣ በዚህ ሰዓትም ሁለተኛዋን ለማግባት የታጨች ናት፡፡ ይህንን መረጃ የሰጠችው የመጀመሪያዋን ስታገባ የገጠማትን በማስታወስ ነው፡፡ ቃለ መጠይቁ የተካሄደው 14/05/2012 ዓ.ም ነው፡፡

[19] ረጅም ሱሪ ማለት ሲሆን ከሙሽሪት ጥሎሽ ጋር አብሮ የሚሰጣት ሲሆን ምናልባት ፈረስ ላይ ስትወጣ ሰውነቷ እንዳይታይ ለመጠበቅ ሲባል እንድትለብሰው ይደረጋል፡፡

በአጭር ጊዜ ጋብቻውን እንዲቀበሉ ከማገዝ ባሻገር የደኅንነት ማስጠንቀቂያም ይሰጣሉ፡፡

### 5.3.6. የተጋቢዎችን ማኅበራዊ ደረጃ ማሳወቅ (ለውጡን ማወጅ/ማረጋገጥ)

የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔዎች አንዱ ተግባር የባለጉዳይን ቀጣይ ሚና ማሳወቅ ወይም ለውጡን ማወጅ ነው፡፡ ለምሳሌ ሙሽሮች በጫጉላ ቤት ሲቆዩና ከጫጉላ ሲወጡ (ሲገለጡ) የሚከናወኑ ሥርዓተ ክዋኔዎች ለውጥ ማካሄዳቸውን ማወጃ ወይም ማረጋገጫ መሆናቸው ይገለጻል፡፡ በዚህ ወቅት የሙሽሮች ልጅነት አብቅቶ ትልቅነት፣ ከጋብቻ በፊት የነበረ ነጻነት አብቅቶ ለማኅበራዊ ሕግና ደንብ መገዛት የሚጀምሩበት መሆኑን በተግባር የሚያሳዩበት ነው፡፡ ለውጡም በአለባበሳቸውና በአጊያጊያጣቸው፣ በንግግራቸው፣ በአረማመዳቸው፣ በስማቸውና በአጠቃላይ እንቅስቃሴያቸው፣ በባሕርያቸው እንዲሁም በአመጋገባቸው ላይ ጭምር በግልጽ ይታያል፡፡

ሙሽሮች ካገቡ በኋላ ስሚኖራቸው አለባበስ የሚከተለውን ሀሳብ ሰጥተዋል፡፡ ሴቷ ነጠላ መልበስ፣ መቀነት መታጠቅ፣ የተለያዩ ጌጣጌጦችን ማድረጓን ትቀጥላለች፡፡ ወንዱም ቀበቶ መታጠቅ፣ ዱላ መያዝ፣ ወግ ያለው ሱሪ መታጠቅ ይጀምራሉ ይላሉ፡፡ ሙሽሮች የመጀመሪያ የሆነውን አንቱታ የሚጀምሩት ሲያገቡ ነው፡፡ አማቶቻቸውን አንቱ በማለት ያናግራሉ፡፡ ቀድሞ የነበረ ዝላይና ሩጫ ይቀርና በወጉ ይራመዳሉ፡፡ እንዲሁም ቀድሞ የነበራቸው ስም ቀርቶ በዳቦ ስም ትጠራለች፡፡ ወንዱም በቁልምጫ ስም ወይም አማች ተብሎ መጠራት ይጀምራል፡፡ አዲሱ ስም የሚጸናው ወይም ተግባራዊ የሚደረገው በአማቶቻቸው ዘንድ መሆኑን ጨምረው አስረድተዋል (አቶ ዘለቀ፣ 25/06/2012 ዓ.ም የተካሄደ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በሌላ በኩል ሙሽሪት ወደ ሙሽራው ቤት ስትሄድ አገልግሏ ውስጥ ከሚደረጉላት የመዋቢያ ቁሶች ጋር የሙያ ቁሳቁሶች (ምላጭ፣ ወስፌ፣ ጥጥና እንዝርት) አብረው ይደረጋሉ፡፡ እነዚህም ቁሳቁሶች የሴት ሚና የሆኑት ስፌት እና ፈትል እንደሚጠብቋት አመላካች ናቸው፡፡ እንዲሁም በእንግድነቷ ከአማቶቿ ምንም ነገር እንዳትጠይቅ፣ ለሙሽርነት ጊዜዋ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች አሟልቶ መላክ እንደሚያስፈልግ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ምክንያቱም በጫጉላ ቤት ቆይታዋ መነጋገር ስለማይፈቀድ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ቀደም ባለው ጊዜ የጫጉላ ቤት ቆይታ ለሁለት ወራት ያህል እንደነበርና በቆይታዋም በእሷ ፈትል የተሰራውን ጋቢ እና ነጠላ ለአማቶቿ የጫጉላ ግላጭ ስጦታ ትሰጥ እንደነበር ይገለጻል፡፡ እንዲሁም የሰፋቻቸው የስፌት እቃዎች እየታዩ ትመረቅ እንደነበር ይገልጻሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር በተለያዩ ሙያዎች ስትፈተን እንደምትቆይ ይነገራል፡፡ የግላጯ ዕለት ወደ ማኅበረሰቡ ስትቀላቀል የሰፋችው ስፌትና የፈተለችው ፈትል እየታየ ትመረቃለች፣ በዘፈንም ትሞገሳለች ይላሉ (ወ/ሮ ቦሰና፣ 12/06/2012 ዓ.ም በተካሄደ ቃለ መጠይቅ)፡፡

> ሙሽሪትማ የፈተለችው፣
> የሸረሪት ድር አስመሰለችው፣
> ሽማኔ ጠፍቶ ማሪያም ሠራችው፡፡ ተብላ ትወደሳለች፡፡

በተለይ በጋብቻ ሽግግር ቀጣዩ ደረጃ በነባራዊው ዓለም፣ በባለጉዳዩ ሕይወት ግልጽ ሆኖ ስለሚታይ ወቅቱ ይህንን በሚያመላክቱ ክዋኔዎችና ገለጻዎች ይታጀባል፡፡ ሙሽራዋ ገና በእናቷ ቤት እያለች በጓደኞቿ የሚከበርላት ምሪ የመፍታት ክዋኔ፣ ልጅነቷ ማብቃቱ ይነገራታል፡፡ የትልቅነት ምልክት የሆነውን መቀነት በማስታጠቅ፣ የሚጠበቅባትን የሚስትነት ሚና ያውጃሉ፡፡ ይህም ሙሽሮች ሲወጡ በሚመረቁት ምርቃት በግልጽ ይታወጃል፡፡ ከተከወኑ ምርቃቶች መካከል የሚከተለው ይጠቀሳል፡፡

> ጋብቻውን የእውነት ያርገው፣ ሕጋቸውን ይባርክልን፣ ይልመዱ፣ ይክበዱ፣ ይውለዱ፣ ሀብታም ከብታም ያድርግልን፣ የተቆረጠላቸውን ሀብት ያቅናው፣ የአያታቸው የቅማታቸው ሀብት በነሱ ላይ ይደር፣ ወልደው ከብደው እንዲኖሩ ያድርግልን፣ ከእናት አባታቸው ፈቃድ አያውጣቸው፣ ቤተ ክርስቲያን እሚሰሩ ሃይማታቸውን እሚጠብቁ ያድርጋቸው፣ ተምረው፣ አድገው፣ ቦታ እሚያስከብሩ፣ ዘመድ እሚጠቅሙ ያድርጋቸው፣ ደም መላሽ ያርጋችሁ፣ እንደ መንግስት መንግስት ያርጋችሁ፣ እንደ ካህን ካህን ያርጋችሁ፡፡[20]

ሙሽሮች ከሰርጋቸው በኋላ ከሚጠብቋቸው ግላዊና ማኅበራዊ ሚናዎች ጋር እንዲስማሙ፣ እርስ በርስ እንዲላመዱ፣ ለፍሬ እንዲበቁ፣ ሰርተው እንዲለወጡ፣ ለቀደሙት እንዲታዘዙ፣ ከፈቃዳቸውም እንዳይወጡ ማስጠንቀቂያ የታከለበት መልካም ምኞት ይገልጹላቸዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያን እንዲሰሩና ሃይማኖታቸውን እንዲጠብቁ፣ ርስታቸውን እና አገራቸውን እንዲያስጠብቁ፣ ለዘመድ እንዲጠቅሙ፣ ደም እንዲመልሱ (ለወንድ ሙሽራ የተመረቀ ነው)[21] የመሳሰሉ በማኅበረሰቡ ዘንድ ቋሚና የጋራ ለሆኑ እሴቶች እንዲገዙ፣ ማህበራዊ ሃላፊነቶችንም እንዲወጡ በአደራ መልክ ይሰጣቸዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር በመንፈሳዊ/ሃይማኖታዊ ሕይወታቸው ካህን፣ በዓለማዊ/ስጋዊ ሕይወታቸው ደግሞ መንግስት እስከመሆን እንዲደርሱ በሰርጋቸው ዕለት ሃላፊነት ይጣልባቸዋል፡፡

## 6. መደምደሚያ

ይህ ጥናት በጋብቻ ወቅት ከሚፈጸሙ ሥርዓት ክዋኔዎች መካከል ከሰርግ ዋዜማ እስከ ጫጉላ ግላጭ ድረስ የሚፈጸሙት ላይ ትኩረት በማድረግ እንዴት የለውጥ መለማመጃ እንደሆኑ መርምሯል፡፡ በዚህ ወቅት የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ዳስ መሥራት፣ የሙሽሪትን ምሪ መፍታት፣ ሙሽራ የመፈተንና ቃል የማስገባት እና የዙረሽ ግቢ ሥነ ሥርዓት በሙሽሪት ወላጆች ቤት የሚፈጸሙ መሆናቸውን መረዳት ተችሏል፡፡

---

[20] ምልከታ፣ ዱምሪ ኪዳነ ምህረት ቀበሌ፣ ቀን 08/07/2012 ዓ.ም

[21] በጃቢ ጠህናን ወረዳ ሴት ልጅን ለመዳር የእሷ ታናሽ የሆነ ወንድሟ ካለ አብሮ ይዳራል፡፡ ሆኖም እንደ ሴቷ ጫናው አይበዛበትም፡፡ ከዚህ ሁኔታ ውጭ ግን ለአቅመ አዳም እስከሚደርስ ይጠበቃል፡፡

ቀጥሎም ሙሽራው ሙሽሪትን ይዞ ወደ ወላጆቹ ቤት ከሄደ በኋላ በጫጉላ ቤት ልዩ ልዩ ሥርዓተ ክዋኔዎች መከናወናቸውን ይቀጥላል፡፡ የመጀመሪያው ለሙሽሪት አጫዋች መመደብ ነው፡፡ በሙሽሪት የጫጉላ ቤት ቆይታ ከሚያጋጥሙና ከሚጠበቁ አዳዲስ ሁኔታዎች ጋር በማላመድ በኩል ትልቅ ድርሻ አላት፡፡ ሙሽሮች በጫጉላ ቤት ምርጥ ምርጥ ምግቦችን እየተመገቡ ይቆያሉ፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው በተለይ ሙሽሪት በግላጪ አምራ እና ውብ ሆና ወደ ማኅበረሰቡ ስለምትቀላቀል እንድትቀላቀል ሲባል እንደሆነ ይነገራል፡፡ ምግቡን የምትሰራላት የሙሽራው እናት መሆኗ የአማትና የምራት ግንኙነት የሰመረ እንዲሆን መሰረት የሚጣልበትም ጭምር ነው፡፡

የሙሽሮችን የጫጉላ ቤት ያማረና የማይረሳ የሚያደርገው ክዋኔ የደገም የተባለው ጨዋታ ነው፡፡ በቦታውና በጊዜው የተገኙ ሰዎች ሁሉ የሚሳተፉበት ሲሆን ዋና ዓላማው ሙሽሮችን ማላመድና ማቀራረብ መሆኑ ይገለጻል፡፡ በዚህ መልክ የቀጠለው የሙሽሮች የጫጉላ ቤት ቆይታ የጫጉላ ግላጭ በተባለ ክዋኔ በይፋ ወደ ማኅበረሰቡ ይቀላቀላሉ፡፡

እነዚህ በሂደት የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ጋብቻ ተጋቢዎች ላይ የሚያስከትለውን ለውጥ በማስተዋወቅና በማዘጋጀት፣ ከለውጡ ጋር በማስማማትና በማለማመድ በኩል የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ብዙ ነው፡፡ ምሪ የመፍታት ሥነ ሥርዓት ሙሽሪትን ለጋብቻው እንዲሁም ከጋብቻው በኋላ ስለሚጠብቋት ግላዊና ማኅበራዊ ሚናዎች መረጃ በመስጠት የቅድመ ጋብቻ ዝግጅት እንድታደርግ ይረዳታል፡፡ ሙሽራን ጥያቄ የመጠየቅና ቃል የማስገባት ሥነ ሥርዓቶችም ሙሽሪት በአማቶቿ ቤት ስትቆይ ደኅንነቷ የተጠበቀ እንዲሆን ዋስትና ይሰጣል፡፡ የዙረሽ ግቢ ሥነ ሥርዓትም ሙሽሪት ከቤተሰቦቿ ለመለየት እንደ መለማመጃ የሚጠቅምና ከሙሽራውም ሆነ ከሚዜዎቹ ጋር ትውውቅ የምታደርግበት አጋጣሚ ነው፡፡ ከዚያም ሙሽሮች በጫጉላ ቤት ሲቆዩ የተለየ ምግም ይመገባሉ፡፡ ለተለያዩ የጤና ወይም የሕይወት ዘመን እክሎች እንዳይጋለጡ በሚልም በቆይታቸው ጥበቃና እንክብካቤ ይደረግላቸዋል፡፡

በመጨረሻም የሙሽርነት ጊዜ አብቅቶ ተጋቢዎች በአዲስ ማንነት ወደ ማኅበረሰቡ የሚቀላቀሉት በጫጉላ ግላጭ ሥነ ሥርዓት መሆኑን ማጤን ተችሏል፡፡ እነዚህ በተከታታይ የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ሙሽሮችን ለጋብቻው ከማዘጋጀት ጀምሮ በየደረጃው ከሚካሄዱ ለውጦች ጋር በማስተዋወቅ፣ በማስማማትና በማለማመድ፣ የሽግግር ወቅቱን በማጀብ፣ ሕክምና በመስጠት፣ ለውጡን በማወጅና በማረጋገጥ በኩል ጉልህ ሚና ያበረክታሉ፡፡

## ማጣቀሻ ጽሑፎች

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ 1993 ዓ.ም፡፡ *የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡* አዲስ አበባ፡፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

Annsel, Nicola. 2005. *Children, Youth Development*. Routledge, Tylor & Francis Group, London and New York.

Bell, Cathrine. 1997. *Ritual Perspectives and Dimensions*. Oxford University Press. New York.

Brana-Shute, R. and Gary, B. 2004. "Death in the Family: Ritual Therapy in a Creole Community". KITLV, *Royal Netherlands Institute Of Southeast Asian and Caribbean Studies*. PP.582–594

Brown, A. Radcliffe. 1952. *Structure and Function in Primitive Society***.** The Free Press, Glencoe.

Canda, Edward. 1988. "Therapeutic Transformation in Ritual, Therapy, and Human Development." *Journal of Religion and Health*, Vol. 27, No. 3 pp. 205-220, Published By Springer.

Creswell, John W. 2007. *QUALITATIVE INQUIRY & RESEARCH DESIGN Choosing Among Five Approaches* (2nd Edition). University of Nebraska, Lincoln, SAGE Publications, Thousand Oaks • London • New Delhi.

Durkheim, Emile. 1965. *The Elementary Forms of the Religious Life.* Translated by J. W. Swain.
New York: Free Press, 1965. Originally published in 1915.

Dorson, Richard. 1972. *Folklore and Folk Liofe: An Introduction*. London, Universty Press.

Dawson, Catherine. 2007. *A Practical Guide to Research Methods* (3rd Edition), British Library Cataloguing in Publication Data.

Firth, Raymond. 1973. *Symbols, public and private.* George Allen & Unwin Ltd, Routledge.

Guday Emirie. 2005. "Early Marriage and Its Effects on Girls' Education in Rural Ethiopia: The Case of Mecha Woreda in West Gojjam, North-Western Ethiopia", Submitted for Doctorate/Doctoral Grade in Ethnology (Social and Cultural Anthropology) to the Faculty of Social Sciences, Georg-August University of Goettingen.

Jensen, Robert. And Thornton, Rebecca. 2003. "Early female marriage in the developing world." Gender and Development, Vol. 11, No. 2, Jul., Gender and Development Published by: Taylor & Francis, Ltd. on behalf of Oxfam GB.

Kitahara, Michio. 1974. A Function of Marriage Ceremony. *Anthropologica, New Series*, Vol. 16, No. 2, pp. 163-175; Canadian Anthropology Society.

Mazama, A. and Asante.M. 2009. Encyclopedia of African Religion (Eds). Sage Publications.

Mikiyas Abera, Ansha Nega, Yifokrie Tefera & Abebaw Addis Gelagay, 2020. "Early Marriage and Women's Empowerment: the Case of Child-Brides in Amhara National Regional State, Ethiopia". *BMC International Health and Human Rights*. PP.20:30.

Molla, M., Berhane, Y. & Lindtjørn, B. 2008. "Traditional Values of Virginity and Sexual Behaviour in Rural Ethiopian Youth: Results from a Cross-Sectional Study". *BMC Public Health* 8 (9). PP. 1-10.

Otoo-Oyortey, N., & Pobi, S. 2003. "Early Marriage and Poverty: Exploring Links and Key Policy Issues". *Gender & Development, 11 (2).* PP. 42 – 51.

Pentkainen, J. 1979. *The Symbolism of Liminality*. Scripta Instituti Donneriani Aboensis.

Raj, A. 2010. When the Mother is a Child: The impact of Child Marriage on the Health and Human Rights of Girls. Archives of Disease in Childhood, 95, 931 –935.

Salamone, Frank (Ed.). 2004. *Encyclopedia of Rites, Rituals and Festivals*. London: Routledge New York.

Segal, Robert, (Ed.), 2006. *The Blackwell Companion to the Study of Religion.* Blackwell Publishing Ltd.

Shambel Tufa, 2020. "Socio-Economic and Cultural Values of Marriage among of Arsi Oromos, in Hethosa Woreda in Oromia Regional State, Ethiopia". *Open Journal of Women's Studies* Volume 2, Issue 2, 2020, PP. 1-8. SRYAHWA PUBLICATIONS.

Silverman, D. (ed.) 1997. Qualitative Research: Theory, Method and Practice. London: Sage.

St. John, Graham. (Ed.). 2008. Victor Turner and Contemporary Cultural Performance New York and Oxford: Berghahn Books.

Tilson, D. & Larsen, U. 2000. Divorce in Ethiopia: The impact of early marriage and Childlessness. Journal of Biosocial Science, 32, 355 – 372.

Turner, Victor, 1969. The Ritual Process Structure and Anti-structure. Itaca New York. Cornell University Press.

-----------. 1968. The forest of symbols፡ Aspects of Ndembu Ritual. United States of America Cornell Universty Press.

UNICEF. 2015. A Profile of Child Marriage in Africa. Retrieved from:

Van Gennep, Arnold. 1960. *The Rites of Passage.* Translated by M. B. Vizedom and G. L. Caffee. Chicago: University of Chicago Press, Originally published in 1909.

Vergroesen L. 2017. The Value of Early Marriage in Amhara Region, Ethiopia: Exploring Local Understandings of Early Marriage in a Context of Active Prevention Activities and a Prohibitive Legal Framework. MSc in Develeopment Study.

Wohabe Birhan. 2014. "Puberty Rites for Girls (Ke Gehaja) Among the Gumuz of Northwestern Ethiopia: Practices, Developmental and Psychosocial Contributions." Semantic Scholar.

Zelalem Desalegne, 2018. An Assessment Study on the Prevalence and Causes of Early Marriage and its Associated Problems on Socio-Economic and Health of Women in Gozamine Woreda East Gojjame Zone Amhara Region.

https://www.unicef.org/protection/57929_58008.html.